

ለማምለጥ በዱር አእዋፍ ፍልሰት የተጠቀመ ይመስለኛል።

አንቷን ደ ሰንት- ኤግዙፔሪ

ታዳጊው ልዑል

ከደራሲው ውኃ ቀለም ሥዕሎች ጋር

ተርጓሚ ዶ/ር ብርሃኑ አበበ

ሸማ ቡክስ



ሻማ ቡክስ

ሻማ ቡክስ
የመ.ሳ.ቁ. 57
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

በጽሑፍ ፈቃድ ወይም በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ አዋጅ ቁጥር 165/1960 ርዕስ 11 የሥነ ጽሑፍና ኪነጥበብ ሥዎች ባለቤትነትን በተመለከተ ከአንቀጽ 1647 እስክ አንቀጽ 1674 በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ከመጽሐፉ አንድ አንቀጽ አንኳን መልሶ ማሳተም፣ መቅዳት ወይም በሌላ መልክ ማሳተምና ማሰራጨት አይፈቀድም።

የመጀመሪያ ኅትመት 2002 ዓ.ም

© ዶ/ር ብርሃኑ አበበ፣ 2002 ዓ.ም

ISBN: 978-99944-0-019-5

የተባበሩት አታሚዎች ኃ. የተ. የግ. ማ.፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የተርጓሚው መቅድም

ታዳጊው ልዑል

አንቷን ሰንት- ኤግዙፔሪ ፈረንሣዊው ኤሮፕላን አብራሪና ደራሲ ይህን ታሪክ የጻፈው በ1943 እ.ኤ.አ ነው። አብራሪው የሞተር ብልሽት ይደርስበትና ኤሮፕላኑን ሰሐራ በረሃ ውስጥ ሲያሳርፍ፣ እዚያ ብቸኝነትን ተዝናንቶ የተቀበለ የሚመስል አንድ ወጣት ያገኛል። ልጁ አንድ ሕዋ አካል ላይ ከአንዲት ጽጌሬዳ ጋር ብቻቸውን ሲኖሩ የጓደኛው ቀብራራነት አስመርሮት አገር ጥሎ የጠፋ ነው። በመሬት ሲጓዝ እግረ መንገዱን ካጋጠሙት የተለያዩ ሰዎች መካከል ንጉሥ፣ የገጸ ምድር ተመራማሪና የጉዳና መብራት አብሪ ሳይቀር ቢገጥሙትም፣ ሁሉም በየበኩላቸው የሚጨነቁት በማይረባ ነገር መሆኑን ይደርስበታል። ሰሐራ ውስጥ ከሚኖር ፌኔክ ከተባለ ድንክ ቀበሮ ጋር ያካሄደው ውይይት ግን የፍቅርን ትርጉም አስገነዘበውና ጽጌሬዳይቱ ትናፍቀው ጀመር። በዚህም ምክንያት ወደ ነበረበት ዓለም ተመልሶ ለመሄድ አንድ እባብ እዲነድፈው አደረገ። ተነባቢነቱ ለሕፃናት እንኳ ምንም ችግር የሌለበት ይህ ደስ የሚል ቅኔ ለበስ ትረካ፣ ያዘላቸው ምስጢራውያን ተምሳሌቶች እንኳን ታዳጊውን አንጋፋውን አንባቢ ሳይቀር በሐሳብ የመመሰጥ ጠባይ ይታይባቸዋል።

ዶ/ር ብርሃኑ አበበ

አንቷን ደ ሰንት- ኤግዙፔሪ


ፈረንሳዊው ኤሮፕላን አብራሪና ደራሲ አንቷን ደ ሰንት- ኤግዙፔሪ ሊዮን ከተማ ሰኔ 29 በ1900 እ.ኤ.አ ተወልዶ በ1944 በኤሮፕላን ተልእኮ ለመፈጸም ወጥቶ የደረሰበት እስከ ዛሬ ሳይታወቅ እንደ ጠፋ የቀረ ታላቅ የብዕር ሰው ነው።

የባሕር ኃይል ትምህርት ቤት መግቢያ ውድድሩን ሲጨርስ፣ ብሔራዊ አገልግሎቱን በአየር ኃይል ውስጥ አጠናቅቆ የንግድ መሥመር ተቀጣሪ ሆኖ ነበር። ብዙም ሳይቆይ በሙከራ ኤሮፕላኖች አብራሪነት ፓሪስ፣ ሳይጎን፣ ኒውዮርክና ቴርደፊ አዲስ በረራዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ በተሳካ ሁኔታ ፈጸመ። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በ1940 በአየር አሰሳ ተመድቦ ከሠራ በኋላ ወደ አሜሪካ ሄዶ ነበር። በ1942 እንደገና ወደ ሰሜን አፍሪካ ተመልሶ ትግሉን ቀጠለ። የአየር ተልእኮ ለመፈጸም ስኮርስ ተነሥቶ እንደ ወጣ የቀረው ሐምሌ 31 ቀን 1944 ነው። አንቷን ድሰንት- ኤግዙፔሪ ከአብራሪነቱ ጐን ለጐን ዓለም አቀፍ ዕውቅና ካተረፉለት ብዙ መጻሕፍት ውስጥ «የደቡብ መልእክተኛ» «የሌሊት በረራ» «የሰዎች መሬት» «የጦር አየር አብራሪ» የተሰኙትን መጥቀስ የደራሲነቱን አድማስ ለማመልከት ይበቃል። ከሁሉም የበለጠ ተቀባይነት ያገኘው ግን በ1943 የደራሲው የመጨረሻ መጽሐፉ «ታዳጊው ልዑል» ነው። ይህ ታሪክ በየቋንቋው ተተርጉሞ ከዓለም የሥነ ጽሑፍ አንጋፋ ውጤቶች መካከል የክብር ቦታውን ይዞ በምስጢራዊ ውበቱ አንባብያንን ከሊቅ እስከ ደቂቅ ሲማርክ ይኖራል።

ለሌዎን ቨርት

ይህን መጽሐፍ ለአዋቂ ስላበረከትኩት ሕፃናትን ይቅርታ እጠይቃለሁ። በቂ ምክንያት አለኝ። ይህ ትልቅ ሰው በምድር ዓለም ከማንም የሚበልጥብኝ ወዳጄ ነው። ሌላው ምክንያቴ ይህ አዋቂ ግለሰብ የሕፃናትን መጽሐፍ ጨምሮ ማናቸውንም ነገር የመገንዘብ ችሎታ ስላለው ነው። ሦስተኛው ምክንያት ይህ አዋቂ ሰው ተርቦና ታርዞ ፈረንሣይ አገር ነዋሪ በመሆኑ በሚገባ መጽናናት ያሻዋል። ይኽ ሁሉ ምክንያት የማይበቃ ከሆነ አዋቂው ግለሰብ ዱሮ ሕፃን በነበረበት ወቅት ይህን መጽሐፍ ለማበርከት ፈቃደኛ ነኝ። አዋቂ ግለሰቦች ሁሉ በጊዜአቸው ሕፃናት ነበሩ የሚያስታውሱት ግን በመጠኑ ናቸው። ስለዚህ አቀራረቤን ላርም።


ለሌዎን ቨርት
ታዳጊ በነበረበት ወቅት



ድሮ ስድስት ዓመት ሲሆነኝ እውነተኛ ታሪኮች በተሰኘ ርእስ ስለ ድንግል ደኖች በተጻፈ መጽሐፍ ውስጥ አንድ ግሩም ሥዕል አየሁ። ዘንዶው አንድ የዱር አውሬ ሲውጥ ነው። የሥዕሉ ግልባጭ ይኸው።


«ዘንዶዎች ሰለባቸውን እንዳለ፣ ሳያኝኩ ይውጣሉ፣ ከዚያም መንቀሳቀስ ይሳናቸውና የበሉትን ሲያዋሕዱ ስድስት ወር ይተኛሉ» ይላል መጽሐፉ።

እኔም ጥቅጥቅ ካለው ጫካ ውስጥ ስለሚካሄደው ነገር ሁሉ ብዙ ካሰላሰልኩ በኋላ ተራዬን በቀለም እርሳስ የመጀመሪያውን ሥዕል ነደፍኩ። ቦጦር አንድ ሥዕሌን ማለት ነው። ይኸንን ይመስላል፣



ሥዕሌን ለአዋቂ ሰዎች አሳየሁና ያስፈራቸው እንደሆነ ጠየቅኋቸው።

እነሱም፣ «ባርኔጣ ምኑ ያስፈራል?» ብለው መለሱልኝ። የኔ ሥዕል የሚያሳየው ባርኔጣ ሳይሆን ዘንዶ ዝሆን ውጦ ሲያዋሕድ ነው። ከዚያ አዋቂዎቹ እንዲገባቸው የዘንዶውን ሆድዕቃ ግልኩላቸው፣ ሁልጊዜ ማብራሪያ ይፈልጋሉ። ሁለተኛው ሥዕሌ ይኸንን ይመስላል፣



አዋቂዎች ክፍት ዘንዶና ድፍን ዘንዶ የምለውን ምሳሌዬን ትቼ ይልቅ ወደ መልክዓ ምድር፣ ወደ ታሪክ፣ ሒሳብና ወደ ሰዋስው እንዳተኩር መከሩኝ። ዕጹብ ድንቅ የሆነውን የሠዓሊነት ሙያ በስድስት ዓመቴ እርግፍ አድርጌ የተውኩት በዚህ ዓይነት ነው። ቁጥር አንድና ቁጥር ሁለት ሥዕሎቼ ተቀባይነት ባለማግኘታቸው ተስፋ ቁርጬ ነው። አዋቂዎቹ ሁልጊዜ አንድ ነገር ካላስረዷቸው አውቀው አይገባቸውም፣ አሁንም አሁንም ማስረዳቱ ደግሞ ልጆችን ያክል።

ከዚያም ሌላ ሙያ ለመምረጥ ተገድጄ ኤሮፕላን ማብረር ተማርኩ። ዓለም ላይ በያለበት በኤሮፕላን ሄጃለሁ። የገጸ ምድር ዕውቀት እውነትም ብዙ ጠቀመኝ። ቻይናን ከአሪዞና ወዲያው ለይቼ ለማወቅ ቻልኩ። ለሊት መንገድ ሲጠፋ በጣም ይጠቅማል። በሕይወቴ ከአያሌ ቁምነገረኛ ሰዎች ጋር ብዙ ጊዜ ለመገናኘት የቻልኩት በዚህ ሁኔታ ነው። አዋቂ ሰዎች ቤት ብዙ ጊዜ ኖሬያለሁ። ከቅርብ አስተውያቸው ነበር። ያም ሆኖ አስተያየቴን እምብዛም አላሻሻለውም።

በመጠኑም ቢሆን አስተዋይ የሚመስለኝ ሰው ሲያጋጥመኝ ባስቀመጥኩት ቁጥር 1 ሥዕሌ እፈትነው ነበር። እርግጥ የሰው ነገር የሚገባው መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። መልሱ ግን

ሁልጊዜም «ባርኔጣ ነው» የሚል ነው። በዚህ ጊዜ ስለ ዘንዶም፣ ስለ ድንግል ደንም፣ ስለ ከዋክብት አላነሣበትም። እሱኑ መስዬ አቀርበዋለሁ። ስለ ካርታ ጨዋታ፣ ስለ ጎልፍ፣ ስለ ፖለቲካና ስለ ክራቫቶች አወራለታለሁ። አዋቂውም ሰው እንደኔ ያለ ልባም ግለሰብ በማግኘቱ ይደሰታል።

፪

የዛሬ ስድስት ዓመት ሰሐራ በረሃ ውስጥ እክል አስካጋጠመኝ ድረስ የልቤን የማነጋግረው ሰው ሳይኖረኝ በብቸኝነት እኖር ነበር። እሞተሩ ውስጥ አንድ ነገር ተሠበረ። ሜካኒክ ሠራተኛና አብረውኝም የሚጓዙ ሰዎች ስላልነበሩ አስቸጋሪውን ጥገና ብቻዬን ለመወጣት ተዘጋጀሁ። የሞት ሽረት ጉዳይ ነበር። የነበረኝ የመጠጥ ውኃ ክምችት ቢበዛ ለሳምንት ብቻ የሚበቃ ነበር።

የመጀመሪያውን ሌሊት ሰው ከሚኖርበት አንድ ሺህ ማይል በሚርቅ አሸዋ ላይ አደርኩ። መርከቡ ሰምጦበት ውቅያኖስ መካከል በታንኳ ከሚንሳፈፍ ሰው የባሰ ብቸኛ ነበርኩ። ሲነጋጋ ያልተለመደ ሰላላ ድምፅ ከእንቅልፌ ሲያስነሳኝ የደነገጥኩት ድንጋጤ ይታያችሁ። ድምፁ

- እባክህ... በግ ሣልልኝ ይላል።
- ምን አልክ?
- በግ ሣልልኝ ...።

መብረቅ እንደ መታው ሰው እመር ብዬ ቆምኩ። ዓይኖቼን አባበስኩ። ተጠንቅቄ አየሁ። አንድ በጣም ልዩ የሆነ ትንሽዬ ልጅ በጽሞና ይመለከተኛል። ከጊዜ በኋላ ልሥለው የቻልኩት መልኩ ይኸውና የኔ ንድፍ ግን በእርግጥ የሱን ወዘና አይደርስበትም። የኔ ጥፋት አይደለም። ስድስት ዓመት ሲሆነኝ

አዋቂዎቹ የሠዓሊነት ሙያዬን አጨናግፈውብኝ ከድፍን ዘንዶና ከክፍት ዘንዶ በስተቀር ሌላ ምንም ነገር መሣል አልተማርኩም። የተከሠተውን ልጅ በአድናቆት ፍጥጥ ብዬ አየው ጀመር። ሰው ካለበት አካባቢ አንድ ሺህ ማይል ርቀት ላይ እንደ ነበርኩ አይዘንጉ። ልጁ ደግሞ ያለበት ቦታ የጠፋው፣ በረሃብ ለሞት የተቃረበ፣ ውኃ ጥም የገደለው፣ በፍርሐት የተሸበረ አይመስልም። እበረሃ መካከል ከሰው መኖርያ አንድ ሺህ ማይልስ ርቀት ላይ የጠፋ ልጅ በጭራሽ አይመስልም።

ቆይቼ ቆይቼ መነጋገር ስችል፣

- ለነገሩ፡ ... እዚህ ምን ልታደረግ መጣህ አልኩት።

- እሱም መልሶ በለስላሳ ድምፅ እንደ ትልቅ ቁም ነገር፣


- እባክህ ... የበግ ሥዕል ሣልልኝ አለኝ።

ምስጢሩ ከመጠን በላይ ከባድ ሲሆን ደፍሮ እምቢ አይባልም። ሰው ከሚኖርበት አካባቢ አንድ ሺህ ማይልስ ርቀት ላይ ለሞት አደጋ በተጋለጥኩበት ሁኔታ አድራጎቴ ትርጉም የሌለው ቢመስለኝም ከኪሴ ወረቀትና የቀለም ብርዕ አወጣሁ። እዚህ ላይ ግን እኔ በመሠረቱ የተማርኩት ገጸ ምድር፣ ሒሳብና ሰዋሰው መሆኑ ትዝ አለኝና ልጁን (እንደ መበሳጨት እያለኝ) ሥዕል መሣል አላውቅበትም አልኩት። እሱ ግን መልሶ፣

- ግድ የለም። የበግ ሥዕል ሣልልኝ።

የበግ ሥዕል ሥዬ ስለማላውቅ ከምችላቸው ሁለት ሥዕሎች አንዱን ሣልኩለት። የድፍኑን ዘንዶ።

- የለም! የለም! ዘንዶ ሆድ ውስጥ ያለ ዝሆን አልፈልግም። ብሎ ልጁ ሲመልስልኝ ጊዜ በጣም ደነቀኝ። ዘንዶ አደገኛ ነው፣ ዝሆንም ቦታ ያጣብባል። እኔ ቤቴ ጠባብ ነው፡ የምፈልገው በግ ነው። የበግ ሥዕል ሣልልኝ። ከዚያ ሣልኩለት። ትክ ብሎ አየና፣






- አይሆንም ! ይኸ በሽታ አጥቅቶታል
- ሌላ ሣልልኝ።
ሣልኩ።
ወዳጄ ከደገኛ ፈገግታ ጋር በአጋ ተቀብሎ፣
- እየው ... ይኸኮ በግ አይደለም
ወጠጤ ነው። ቀንድ አለው።
ሥዕሌን መልሼ ሣልኩ፡
አሁንም እንደ ፊተኞቹ ሁሉ ተቀባይነት
ሳያገኝ ቀረ።



- ይኸኛው አርጅቷል። እኔ እምፈልገው
ብዙ ዓመት የሚኖር ነው። ታዲያ ትእግሥት
አጣሁና ሞተሬን መፍታት ለመጀመር ቸኩዬ
ነበርና ይኸንን ሥዕል ጫር ጫር አደረግሁ። እናም
- ይኸ ሣጥኑ ነው። እውስጡ የምትፈልገው
በግ አለ ብዬ ጣል አደረግሁለት።



ግን ወጣቱ ዳኛዬ ፊቱ ወገግ ሲል
አየሁና በጣም ገረመኝ።
- ልክ እንደዚህ ነው የምፈልገው!
ለበጉ ብዙ ሣር የሚያስፈልግ ይመስልሃል?
- ለምን?
- ቤቱ ጠባብ ስለሆነ ነዋ ...
- ሳይበቃው አይቀርም። የሰጠሁህ በግ አነስተኛ ነው።
ወደ ሥዕሉ ጐንበስ አለና፣



- ይህን ያህል ትንሽ አይደለም ... ዓየኸው! እንቅልፍ ይዞታል ...::

ከታዳጊው ልዑል ጋር የተዋወቅነው በዚህ ዓይነት ነው::

፫

ከየት እንደ መጣ ለማወቅ ብዙ ጊዜ ፈጅቦኝ:: ብዙ ጥያቄ የሚያቀርብልኝ ታዳጊ ልዑል የኔን ጥያቄዎች ፈጽሞ የሚያዳምጥ አይመስልም ነበር:: እንደ ዘበት የሚወረውራቸው አንዳንድ ቃላት ናቸው ቀስ እያለ ሁሉንም እንዳውቀው የረዱኝ:: ለምሳሌ ኤሮፕላኔን መጀመሪያ ሲያይ (አሳሳሉ በጣም ስለሚያስቸግረኝ ኤሮፕላኔን አልሥለውም) እንዲህ ብሎ ጠየቀኝ:

- ያ ነገር ምንድነው?

- ያ ነገር ዕቃ አይደለም:: ይበራል:: ኤሮፕላን ነው:: የኔ ኤሮፕላን ነው::

እናም መብረር እንደምችል ስነግረው ኩራት ተሰማኝ::

አሁን ድምፁን ከፍ አድርጎ:

- እንዴት! ከሰማይ ነው የወደቅኸው!

- አዎ አልኩ በትሕትና::

- ወይኔ! ይገርማል...::

ታዳጊው ልዑል ደስ የሚል ሣቅ ከት ብሎ ሲሥቅ በጣም ተበሳጨሁ:: የደረሰብኝን መከራ በቁም ነገር እንዲያይልኝ እፈልጋለሁ:: ከዚያም ቀበል አድርጎ፣



- እንግዲያው አንተም ከሰማይ ነዋ የወረድኸው? ከየትኛው የሕዋ አካል ነው?

እዚህ የመገኘቱ ምስጢር ወዲያው ውልብ አለብኝና ሳይጠብቀው፣

- እንግዲያው አንተ ከሌላ የሕዋ አካል ነዋ የወረድከው?

ብዬ ጠየቅሁት ግን መልስ አልሰጠኝም። ኤሮፕላኔን እየተመለከተ በቀስታ ራሱን በመነቅነቅ የአዎንታ ምልክት አሳየኝና፣

- እርግጥ እዚህ ውስጥ ሆነህ ከሩቅ መምጣት አትችልም...። እናም በሐሳብ ተውጠ ብዙ ቆየ። ከዚያም የኔን በግ ከኪሱ አወጣና ሀብቱን በተመስጠ ያስተውል ጀመረ።

«ሌሎች የሕዋ አካላት» በማለት የምስጢሩን ጫፍ ሲገልጥልኝ ምን ያህል እንደ ከነከነኝ ይታያችኋል። ጠለቅ ብዬ ለማወቅ በመሞከር፣

- ማሙዬ ከየት ነው የመጣኸው? አገርህ የት ነው? በጌን የት ልትወስደው ነው?

በዝምታ አስላስለና፣

- የስጠኸኝ ሣጥን ጥሩነቱ ማደሪያ ቤት ይሆነዋል አለኝ።

- ነው እንጂ። ጥሩ ልጅ ከሆንክ ቀን ቀን ለማሠር የምትገለገልበት ገመድ እስጥሃለሁ። ችካልም።

የቀረበለት ሐሳብ ታዳጊውን ልዑል የረበሸው ይመስላል።

- ማሠር? ምን ዓይነት አስተሳሰብ ነው!

- ካላስርከውኮ የትም ሲዞር አንድ ቀን ይጠፋል። ...።

ታዳጊው ልዑል ቢ612 በተባለው የዓውደ ፀሐይ ሕዋ አካል ላይ።

ወዳጇ እንደገና ከት ብሎ ሣቀ።

- የት ይሄዳል ብለህ ነው?

- የትስ ቢሆን። ቀጥ ብሎ ፊትለፊት ቢሄድስ? ...።

እዚህ ላይ ታዳጊው ልዑል በቁም ነገር፣

- ግድ የለም፣ ቤቴ በጣም ጠባብ ነውኮ!



ታዳጊው ልዑል ቢ612 ቡተባለው የዓውደ
ፀሐይ ሕዋ አካል ላይ።

ከዚያም እንደ መተከዝ ያለው ይመስላል፣
- ፊት ለፊት ተሂዶ የትም አይደረስ አለ።

፬


እንግዲህ ሁለተኛ በጣም ትልቅ ነገር ማወቄ ነው። የልጁ የትውልድ ሕዋ አካል ከአንድ ቤት እምብዛም አይሰፋ ማለት ነው! በዚህ ብዙም አልደነቀኝ። እንደ መሬት እንደ ጁፒቴር እንደ ማርስና እንደ ቬኑስ ካሉት ስም ከወጣላቸው ታላላቅ ከዋክብት ውጪ አንዳንድ ጊዜ በጣም ከማነጣቸው የተነሣ በመነጥር ለመየት የሚያስቸግሩ በመቶዎች የሚቈጠሩ ሕዋዎች አሉ። የሥነ ከዋክብት ተመራማሪ አንዱን ሲያገኘው የአኃዝ ስም ያወጣለታል።

ለምሳሌ ትንሽዟን «የሕዋ አካል 325 ይላታል።» ታዳጊው ልዑል ቢ612 ከተባለው ሕዋ አካል ለመምጣቱ አንዳንድ አስተማማኝ ምክንያቶች አሉኝ። ይኸ ሕዋ አካል በመነጽር የታየው አንድ ጊዜ ብቻ እ.ኤ.አ. በ1909 በአንድ ቱርካዊ የከዋክብት ተመራማሪ ነው።

ተመራማሪውም በወቅቱ ለሥነ ከዋክብት ዓለም አቀፍ ጉባዔ ግኝቱን በሰፊው አሳውቆ ነበር።








ነገር ግን በሀገረሰብ ባህላዊ ልብሱ ምክንያት ማንም አላመነውም ነበር። አዋቂዎቹ ይሸው ናቸው።

እንደ ዕድል ሆኖ ለሕዋ አካል ቢ612 ዝና የበጀው አንድ የቱርክ አምባገነን ሕዝቡን እንደ ፊረንጅ ካልለበስክ ይመት በቃ እፈርድብሃለሁ ብሎ ማስገደዱ ነው። የሥነ ከዋክብቱ ተመራማሪ በ1920 እ.ኤ.አ. ዘናጭ ልብስ ለብሶ ማስረጃውን በድጋሚ ሲያቀርብ ጊዜ ሐሳቡን ሁሉም ተቀበሉት።

የሕዋ አካል ቢ612 ታሪክን በዝርዝር መተረኬና አጋዙንም መግለጼ በአዋቂዎቹ ሰዎች ምክንያት ነው፡ አዋቂዎቹ አጋዞች ይወዳሉ። ስለ አዲስ ወዳጅ ያወሩላቸው እንደሆነ ፍሬ ነገሩን አይጠይቁም። «ድምፁ እንዴት ነው? የሚወደው ጨዋታ ምንድነው? ቢራቢሮዎች ይሰበስባል?» አይሉም። እነሱ የሚጠይቁት «ስንት ዓመቱ ነው? ስንት ወንድሞች አሉት? ክብደቱ ስንት ነው?» ብለው ነው። ያወቁት የሚመስላቸው ያ ሲሆን ብቻ ነው። አዋቂዎቹን ሰዎች «ቀለሙ ጽጌረዳ በመሰለ ጡብ የተሠራ፣ መስኮቱ በቁርጤ አበባ የተጌጠ፣ ጣራው ላይ እርግቦች የሠፈሩበት ቆንጆ ቤት አየሁ» ቢሏቸው ቤቱ በዓይነ ኅሊናቸው አይታያቸውም። «መቶ ሺህ ፍራንክ የሚያወጣ ቤት አየሁ





ማለት አለብዎት:: ያንጊዜ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በአድናቆት፣ «እንዴት ያምር!» ይላሉ::

በተመሳሳይ፣ «ታዳጊው ልዑል ያምራል፣ ይሥቃል በግም ይፈልግ ነበር፣ ይኸ ሁሉ መኖሩን ያስረዳል:: በግ እፈልጋለሁ ካለ የራሱን መኖር አረጋገጠ ማለት ነው» ቢሏቸው፣ በትከሻቸው ምልክት አሳይተው እንደ ሕፃን ያይዎታል! «ልጁ የመጣው ከሕዋ አካል ቢ612 ካሏቸው ግን በጉዳዩ ያምኑበትና እርስዎም ከጥያቄዎቻቸው ይገላገላሉ:: የነሱ ነገር ይኸው ነው:: ቂም መያዝ አያሻም:: አዋቂዎቹን በተመለከተ ልጆች ጠባያቸውን አውቀው መቻል አለባቸው::

እርግጥ፣ እኛ ሕይወትን የተገነዘብነው ግን፣ አኃዞችን እንደ ቀልድ ነው የምናያቸው! ይህንን ታሪክ በተረት መልክ ማቅረብ በወደድኩ ነበር:: እንዴት ቢሉ!

አንድ ጊዜ ከርሱ ትንሽ በምትበልጥ የሕዋ አካል ላይ የሚኖር ወዳጅ ማበጀት የሚፈልግ አንድ ታዳጊ ልዑል ነበር:: የሕይወት ዘይቤ ለሚገባቸው ሰዎች ይህ አቀራረብ እውነት መስሎ በታያቸው ነበር::

ምክንያቱም መጽሐፌን በቀላሉ ቢያነቡት አልወድም:: እነዚህን ትዝታዎቼን ሳወሳ የሚሰማኝ ሐዘን ቀላል አይደለም:: ወዳጄ በጉን ይዞ ከሄደ እነሆ ስድስት ዓመት ሆኗል:: እዚህ በጽሑፍ ላቀርበው የምሞክረው እንዳልረሳው ብዬ ነው:: ወዳጅ ወዳጁን ሲረሳ አሳዛኝ ነገር ነው:: ሰው ሁሉ የልብ ወዳጅ የለውም:: ትኩረታቸውን አኃዞች ላይ ብቻ እንደ ጣሉት አዋቂዎች ልሆን እችላለሁ:: ለዚህም ነው አንድ ሣጥን ቀለምና እርሳሶች የገዛሁት:: ድፍን ዘንዶና ክፍት ዘንዶ ያውም በስድስት ዓመቱ ከመሳሉ በስተቀር ሌላ ምንም ላልሞከረ ሰው አሁን በዚህ ዕድሜው ወደ ሥዕል መመለስ ከባድ ነው! እርግጥ፣ በተቻለ መጠን አብነቱን የሚመስሉ ሥዕሎች ለመሳል እሞክራለሁ:: ይሳካልኛል ብዬ ሙሉ በሙሉ አላምንም:: አንዱ

ንድፍ ይዋጣል፣ ሌላው አልመስል ይላል። እቁመቱም ላይ ትንሽ እሳሳታለሁ። አሁን እዚህ ላይ ታዳጊው ልዑል በጣም አድጓል። እዚያኛው ላይ በጣም አንሷል። እልብሱም ቀለም ላይ እያመነታሁ ነው። እንደ ነገሩ በዳስሳ ወዲያ ወዲህ እነካካዋለሁ። በመጨረሻ አንዳንድ ዋና ነጥቦች ላይ መሳሳቴ አይቀርም። ያንን እንግዲህ ይቅርታ ያደርጉልኛል። ወዳጄ ፊጽሞ ማብራሪያ አይሰጥም ነበር። ምናልባት እንደሱ ዓይነት የሆንኩ ይመስለው ይሆናል። የሚያሳዝነው ነገር እኔ እሣጥን ውስጥ ያሉ በጎችን ማየት አይችልም። በመጠኑ እንደ ትልልቆቹ ሰዎች ሳልሆን አልቀርም። ሳላረጅ አልቀርም።

፫

በየቀኑ ስለ ሕዋ አካል፣ ስለ በረራ፣ ስለ ጉዞ አንዳንድ ትምህርት አገኝ ነበር። በሐሳቤ መካከል እየመጣ ቀስ በቀስ ነበር የሚገባኝ። እንዲህ እያልኩ ነው በሦስተኛው ቀን የወርካዎችን ፍዳ የደረስኩበት።

አሁንም ይህንን ለማወቅ የቻልኩት በበጉ ምክንያት ነው። ታዳጊው ልዑል ከባድ ጥርጣሬ እንደ ገባው ሰው በድንገት፣

- በጎች በእርግጥ ቁጥቋጦ ይበሉ የለም? ሲል አበክሮ ጠየቀኝ።

- አዎ በእርግጥ ይበላሉ።

- ጎሽ! ደስ አለኝ።

የበጎች ቁጥቋጦ መብላት ለምን ይህን ያህል ቁም ነገር እንደ ተሰጠው ሊገባኝ አልቻለም ነበር። ታዳጊው ልዑል ግን ቀጠል አድርጎ፡

- ስለዚህ ወርካዎችንም ይበላሉ? አለኝ።

ወርካዎች የቤተክርስቲያን ሕንፃ የሚያካክሉ ዛፎች ናቸው እንጂ ቁጥቋጦዎች አለመሆናቸውንና በዚህም ላይ የዝሆን

መንጋ እንኳን ይዞ ቢሄድ መንጋው አንዱን ወርካ በልቶ እንደማይጨርስ ታዳጊውን ልዑል አስረዳሁት።

የዝሆኑ መንጋ ጉዳይ ታዳጊውን ልዑል አሳቀው።

- አንዱን ባንዱ ላይ ማደራረብ ያስፈልግ ይሆናል...።


ግን አስተዋይነት በተሞላ አባባል እንዲህ አለ፣

- ወርካ ከማደጉ በፊት ለጋ ሆኖ ነው የሚጀምረው።

- ልክ ነው! ግን ያንተ በጎች ለጋ ወርካ እንዲበሉ የምትሻው ለምንድነው?

ሲመልስልኝ ልክ እንደማያከራክር ነገር፣ «ታዲያስ! ምን ማለትህ ነው!» አለኝ። እኔም ችግሩን አስቤ ለመገንዘብ ከባድ የአእምሮ ጥረት አስፈለገኝ።

በእርግጥም እታዳጊው ልዑል ሕዋ አካል ላይ በማናቸውም ሕዋ አካላት እንደሚኖረው ጥሩ ሣርና አረም አለ። ስለዚህ ጥሩ ሣር ጥሩ ዘር መጥፎ ሣርም መጥፎ ዘር አለው ማለት ነው። ዘሮቹ ግን በዓይን አይታዩም። አንዷ የቀበጠች ቅንጣት እስክትነቃ ድረስ በከርሰ ምድር ምስጢር ውስጥ ተሠውረው ይኖራሉ። ያቺ ቅንጣት እየተንጠራራች ስትፈራ ስትቸር ውብ የሆነ ሰው የማይነካ ለጋ ቀንበጧን አስቀድማ ወደ ሰማይ ትገፋለች። የፍጅል ወይም የጽጌረዳ ቀንበጥ ከሆነ እንደ ልቡ እንዲበቅል መተው ይቻላል። አረም ከሆነ ግን ዘሩ እንደ ታወቀ ወዲያው መንቀል ያስፈልጋል።



ይህ ሲሆን በታዳጊው ልዑል ሕዋ አካል ላይ በጣም አስቸጋሪ አዝርእት ነበሩ...።



የወርካ አዝርእት ናቸው። የሕዋ አካሉን መሬት ወረውታል። ዋርካ ደግሞ ከዘገዩ ለመገላገል ፈጽሞ አይቻልም። ሕዋ አካሉን በሙሉ ያጣበዋል።

ሥሮቹ ዘልቀው ይሰረስሩታል። ሕዋ አካሉ ካነሰና ዋርካዎቹ ከበዙ ሕዋ አካሉን ያፈነዱታል።

«ታዳጊው መስፍን ቆየት አለና ሥርዓቱን የማክበር ጉዳይ

ነው አለኝ:: ጧት ራስን ካጸዱ በኋላ ሕዋ አካሉንም በጥንቃቄ ማጽዳት ያስፈልጋል:: የወርካ ተክል በቡቃያነቱ ከጽጌረዳ ተክል ጋር በጣም ስለሚመሳሰል ገና ልዩነቱ ሲታወቅ ሥራዬ ብሎ መንቀል ያሻል:: ሥራው እጅግ ያስለቻል እንጂ አያስቸግርም::»

አንዱን ቀን ይህ ነገር አገሬ ልጆች ራስ ውስጥ ደኅና አድርጎ እንዲገባ ጥሩ ሥዕል ተግቼ እንድሠራላቸው መከረኝ:: «መንግድ የተጓዙ ዕለት ሊጠቅማቸው ይችላል አለኝ:: አንዳንድ ጊዜ ሥራን ለነገ ማሳደር አይጐዳም:: ወርካን በተመለከተ ግን ሥራውን ማሳደር ታላቅ አደጋ ነው:: አንድ ሰነፍ ግለሰብ ይኖርበት የነበረ ደሴት አስታውሳለሁ...:: ሦስት ችግኞችን ቸል ብሎ ነበር::»

ታዳጊው ልዑል የነገረኝን እየተከተልሁ ያንን ሕዋ አካል ሣልኩት:: አነጋገሬ እንደ ሥነ ምግባር አስተማሪ እንዲሆን አልፈለግም:: ነገር ግን የዋርካን አደጋ ሰው ስለማያውቀውና አንድ ሕዋ አካል ላይ እግር ጥሎት የሚወድቅ ሰው ሊደርስበት የሚችለው ችግር እጅግ ከባድ ስለሆነ ለአሁን ብቻ ከንግግር መቆጠቤን ትቼ የምናገረው ነገር አለኝ:: «ልጆች! ወርካ ተጠንቀቁ::» ይኸንን ሥዕል ብዙ የደከምኩበት እንደኔ ለረዥም ጊዜ ባለማወቅ ይጋፈጡት ከነበረው አደጋ እንዲጠነቀቁ ነው:: የምሰጠው ትምህርት አስፈላጊ ነው:: «እዚህ እመጽሐፍ ውስጥ ወርካውን የሚያህል ሌላ ትልቅ ሥዕል ለምን አልገባም ትሉ ይሆናል:: መልሱ ቀላል ነው፣ ሞክሬ ስላቃተኝ ነው:: ወርካዎቹንም የሣልኩት የጭንቀቱ ስሜት ገፋፍቶኝ ነው::



ወርካዎች



፭

አይ ታዳጊው ልዑል ትካዜ የተሞላ ኑሮህን እንዴት እንደምትገፋው ቀስ እያለ እየገባኝ ነው። ከጀንበር መጥለቅ ውበት በስተቀር ሌላ ምንም የሚያዝናናህ ነገር ሳታይ ለረዥም ጊዜ ኖረሃል። ይኸንንም አዲስ ሁኔታ ለማወቅ የቻልኩት በተገናኘን በአራተኛው ቀን ጧት፣

- ጀንበር ስትጠልቅ ማስተዋል ደስ ይለኛል... ስትለኝ ነው።

- ግን መጠበቅ ያስፈልጋል።

- የሚጠበቀው ምንድነው?

- ጀንበር እስክትጠልቅ።

በፊት በጣም እንደ መገረም አልክና ከዚያ መልስህ በራስህ ሚዛህ፣ ቀጥለህም፣

- አሁንም አገሬ ያለሁ ይመስለኛል! አልክኝ።

እርግጥ አሜሪካን አገር እኩለ ቀን ሲሆን እንደሚታወቀው እፈረንሣይ አገር ጀንበር ትጠልቃለች። ጀንበር ስትጠልቅ ለማየት በአንዲት ደቂቃ እፈረንሣይ አገር መድረስ ብቻ ነው። የሚያሳዝነው ፈረንሣይ አገር በጣም እሩቅ መሆኑ ነው። አንተ ግን አነስተኛ የሕዋ አካልህ ላይ ሆነህ ወንበርህን ጥቂት እርምጃዎች ፈቀቅ ማድረግ ብቻ ነው። ከዚያ የጀንበሯ መጥለቅ እንደ ልብህ ይታይሃል።

- አንድ ቀን አርባ አራት ጊዜ ጀንበር ስትጠልቅ አየሁ!

ትንሽ ቆየህና ንግግርህን በመቀጠል፣

- ታውቃለህ... ሐዘን ሲያጠቃህ ጀንበር ስትጠልቅ ማየት ደስ ይላል...።

- አርባ አራት ጊዜ ያየህ ዕለት በጣም አዝነህ ነበረ ማለት ነው?

ታዳጊው ልዑል መልስ አልሰጠም።

፯

በአምስተኛው ቀን አሁንም በበጉ የተነሣ ሌላ የታዳጊው ልዑል የሕይወቱ ምስጢር ተገለጸልኝ። ለረዥም ጊዜ በዝምታ ሲያወጣ ሲያወርድ የነበረውን ጥያቄ ዳር ዳር ሳይል በድንገት አቀረበልኝ፡

- በግ ቁጥቋጦ ከበላ አበባም ይበላል ማለት ነው?
- በግ ያገኘውን ሁሉ ነው የሚበላው።
- እሾሃም አበቦችም ቢሆኑ?
- አዎ። እሾህ የሚያበቅሉ አበቦችም ቢሆኑ።
- ታዲያ እሾሁ ምን ፋይዳ አለው?

እኔ ምን አውቃለሁ:: አንድ በጣም የጠበቀ የሞተር ቡሌን ለመፍታት በመታገል ላይ ነኝ:: ብልሽቱ ከባድ እንደ ሆነ እየታየኝ ስጋት ይዞኛል፣ በዚህ ላይ የሚጠጣ ውኃ መቀነስ የባሰ ችግር እንዳያስከትል እየፈራሁ ነው::

- እሾህ የሚጠቅመው ለምንድነው?

ታዳጊው ልዑል አንድ ጊዜ ጥያቄ ካቀረበ እሺ ብሎ አይለቅም ቡሌኑ አበሳጭቶኝ ስለነበረ አፌ እንዳመጣ ስመልስለት፣

- እሾህ የአበባዎች ክፉት ከመሆኑ በስተቀር ሌላ ሚና የለውም::

- ኧረ እባክህ!

- ጸጥ አለና እንደ ተቆጨ ሰው፣

- አላምንህም! አለኝ:: አበባዎች ደካሞች ናቸው፣ የዋሆች ናቸው:: እንዳቅማቸው ይግደረደራሉ:: እሾህ ስላላቸው አስፈሪ የሆኑ ይመስላቸዋል...::

መልስ አልሰጠሁም:: ልክ በዚህ ጊዜ ይኸ ብሌን እምቢ ካለ በመዶሻ አፈልሰዋለሁ::

ታዳጊው ልዑል እነደገና ረበሸኝ፣

- አንተ አበቦች ... ይመስልሃል?

- አይ! አይ! አላምንበትም እንደ መጣልኝ መለስኩለት:: እኔ አሁን ቁም ነገር ያለው ሥራ እየሠራሁ ነው::

በድንጋጤ አየኝ::

- ቁም ነገር?

መዶሻ ይዤ፣ ጣቶቼን ግራሶ አቆሸሿቸው፣ ለሱ በጣም አስቀያሚ ሆኖ የታየው አንድ ጥቁር ነገር አጐንብሼ ሳጠና ተመለከተኝ::

- አነጋገርህ ነፍስ እንዳወቀ ሰው ነው::

አፈር አልኩ፡ እሱ ግን ምንም ሳይራራልኝ፣

- ትዘባርቃለህ ... ተምታቶብሃል!

በእውነት በጣም ተበሳጭቶ ነበር:: ወርቅማ ጐፈሬውን አየር

ላይ አወራጨ። አንድ ቅላቱ ደም የሚመስል ሰው ያለበት ሕዋ አካል አውቃለሁ። ያ ሰው አበባ አሽትቶ አያውቅም። ኮከብ አይቶ አያውቅም። ሰው ወዶ አያውቅም። ድምር ከመደርደር በቀር ሌላ ሥራ ሠርቶ አያውቅም። ቀኑን ሙሉ እንዳንተ፣ «እኔ ቁም ነገረኛ ሰው ነኝ! እኔ ቁም ነገረኛ ሰው ነኝ» እያለ ስለሚውል ልቡ በኩራት ያብጣል። ግን እንጉዳይ ነው እንጂ ሰው አይደለም።

- ምንድነው ያልከው?

- እንጉዳይ!

ታዳጊው ልዑል በዚህ ጊዜ
ፊቱ በቀላ ከሰል መስሎ ነበር።

- አበቦች እሾህ በማውጣት ሚሊዮን
ዓመት አስቈጥረዋል። ቢሆንም
በጎች አበባ ሲበሉ ሚሊዮን ዓመት
ሆኗቸዋል። ምንም ላይጠቅማቸው እሾክ
ለማውጣት ይህን ያህል ለምን እንደ ደከሙ
ለመገንዘብ መሞከር ዋጋ የለውም። የበጎችና
የአበባዎች ጦርነት ፋይዳ የለውም? ቁም ነገሩና

አስፈላጊነቱ አንድ ፊቱ ፍም የሚመስል ወፍራም ሰው ከሚያረድረው ድምር አይበልጥም? ከኔ ሕዋ አካል ውጪ ዓለም ላይ የትም የማይገኘውን ብርቅዬ አበባ በጉ ዝም ብሎ ጧት ተነሥቶ የሚያደርገውን ሳያውቅ ጨርግዶ ቢያወድመው ይኸ ከባድ ጉዳይ አይደለም?

ፊቱ ቀይ ሆነና ወዲያው በመቀጠል፣

- በብዙ ሚሊዮን በሚቈጠሩ ከዋክብት መካከል አንድና ብቸኛ የሆነ አበባ የሚወድ ሰው ደስ እንዲለው ከዋክብቱን ማየት ብቻ ይበቃዋል። «እነዚያ መካከል አንዱ ላይ የኔ አበባ አለ። በጉ አበባውን ከበላው ግን ከዋክብቶቹ ሁሉ ጨለመበት ማለት ነው! ይኸ ከባድ ጉዳይ አይደለም?»

ሌላ ምንም ሊያክልበት አልፈለገም። በድንገት እንባ ተናነቀው። መሸቶ ነበር። እኔ መሣያዎቼን ጥዬ ነበር። መዶሻውም ቡሎኑም ውኃ ጥሙም ሞቱም ደንታ አልሰጡኝም። አንድ ኮከብ ላይ እኔ ሕዋ አካል መሬት ላይ አንድ ታዳጊ ልዑል ማጽናናት ነበረብኝ። እቅፍ አድርጌ እሽሩሩ «የምትወደው አበባ ለምንም ዓይነት አደጋ አልተጋለጠም፤... ለበግህ ልባብ እሥልልሃለሁ» አልኩት። ለአበባህም ጥሩር እሥልልሃለሁ... እናም...» የምለው ጠፋኝ። ግራ ገባኝ። እንዴት ልድረስበት፣ እንዴት ልቡን ላግኘው፡... የእንባ ነገር ምስጢሩ ብዙ ነው።

፰

ጊዜ ሳይፈጅብኝ ያንን አበባ በተሻለ ሁኔታ ለማወቅ ቻልኩ። ታዳጊው ልዑል ሕዋ አካል ላይ ቦታ የማይወስዱና ሰው የማያስቸግሩ በአንድ ዙር ቅንጣቶች የተጌጡ ጥራት ያላቸው አበባዎች ሁልጊዜም ነበሩ። ሟች እመስኩ ላይ ብቅ ይሉና ሲመሽ ጥፍት ይሉ ነበር። ያ ብርቅዬ አበባ ግን የበቀለው ከየት እንደ መጣ ካልታወቀ ዘር ነበርና ያችን ከሌሎቹ የተለየችውን ቡቃያ ታዳጊው ልዑል ከቅርብ ይጠብቃት ነበር። አዲስ የወርካ ዘር ልትሆን ትችላለች። ትንሿ ቁጥቋጦ ግን ወዲያው ማደጉን ተወችውና ለማበብ ትዘጋጅ ጀመር። ታዳጊው ልዑል በጣም ትልቅ የሆነ እምቡጥ ተመቻችቶ ሲቀመጥ እያየ ተአምራዊ ክስተት ይወጣዋል ብሎ ተስፋ ሲያደርግ አበባዋ ግን አረንጓዴ ክፍል ውስጥ ተሸሽጋ መሽሞርሞሯን በረጅሙ ተያያዘችው። ቀለማቱን ስትመርጥ በጥንቃቄ ነበር። ስትለብስ በእርጋታ ቀንበጦቿን የምታስተካክለውም አንድ በአንድ ነበር። ስትፈካ ቀንበጦቿ እንደ ጓዟማ ተጨማደው እንዲወጡ አትፈልግም ውበቷ ሙሉ በሙሉ ሲያንጸባርቅ ከማሳየት በቀር ሌላ ፍላጎት

አልነበራትም። አዎ፣ ይኸውልህ! በጣም ሽቅርቅር ናት። በምስጢር ስትዋብ ብዙ ቀንና ሌሊት ፈጀባት። እናም አንድ ቀን በሚት ልክ ጎሕ በሚቀድበት ሰዓት ብቅ አለች።

ከዚያም በስፍተኛ ጥንቃቄ ትሠራ የነበረችው እያዛጋት፣

«እፎይ! ገና መንቃቴ ነው... ይቅርታዎን... ጸጉሬንም ገና አልተበጠርኩም» አለችው።

ታዳጊው ልዑል አድናቆቱን መቈጣጠር አቃተውና፣

- አቤት ማማርዎ! አላት።

- አይደል? አለችው ቀስ ብላ። የተወለድኩትም ከፀሐይቱ ጋር ነው...።

ታዳጊው ልዑል ትሕትና እንደማያጠቃት በትክክል ግን በጣም ታባባለች!

- ቀበል አደረገችና የቍርስ ሰዓት የደረሰ ይመስለኛል፣ እባክዎ እንዳይረሱኝ...።

ታዳጊው ልዑልም እፍር ብሎ፣

አንድ አትክልት ማጠጫ ሙሉ ጥሩ ውኃ አመጣና አቀረበላት።

በመጠኑም ቢሆን ጥርጣሬ

በሚያይበት ከንቱነቷ ገና ከመነሾው አሠቃይታው ነበር።

ለምሳሌ አንድ ቀን ስለ አራቱ እሾሆቿ ታዳጊውን ልዑል፣

- ነብሮቹ መጥተው እስቲ በጥፍራቸው ይሞክሩኝ! አለችው።





- ታዳጊው ልዑል፣ «እኔ ሕዋ አካል ላይ ነብር የለም፣ ነብር ደግሞ ሣር አይበላም። ብሎ መለሰላት።

- እሷም በለስላሳ ድምፅ፣ «እኔኮ ሣር አይደለሁም» አለችው።

- ይቅርታዎን ...

- ነብር ምኑም ምኑም አያስፈራኝ፣ እኔ በጣም የምጠላው ተባራሪ ንፋስ ነው። ከለላ የሚሆነኝ ግርዶሽ የለዎትም? «የተባራሪ ንፋስ ጥላቻ ብሎ ነገር...። ለአንድ ተክልስ ዕድል ማጣት ነው» አለ ታዳጊው ልዑል። «ይቺ አበባ ችግር አለባት...»

- ማታ ክዳን ይደፋብኛል፣ አገርዎ በጣም ይበርዳል፣ አቀማመጡ ትክክል አይደለም። የኔ አገር... ንግግሯን አቋረጠች።

የመጣችው ገና ጥሬ ዘር ሆና ነው። ስለ ሌላው አገር ምንም ማወቅ ሳትችል ማለት ነው። እንዲህ ያለ የሞኝ ውሸት ስታውጠነጥን ስለ ደረስኩባት አፍራ ሁለት ሦስት ጊዜ እንደ መሳል አለች፣ ታዳጊውን ልዑል ጥፋተኛ ለማድረግ።

- ግርዶሹን እንዴት አደረጉልኝ?



- ላመጣው ነበር ንግግርዎን ይጨርሱ ብዬ ነው።

እንዲጸጽተው ብላ ሳሏን አውቃ አከረረችው። ይኸ ሲሆን ታዳጊው ልዑል ፍቅሩ ቀና ይሁን እንጂ



አበባይቱ ወዲያው ጥርጣሬ ሳታሳድርበት አልቀረችም። ለፍሬቢስ አነጋገሯ ዋጋ እየሰጠ በጣም አዝኖ ነበር።

«ባልሰማት ይሻለኝ ነበር። አበቦችን ማየትና ማሽተት ነው እንጂ መስማት በፍጹም አያስፈልግም። የኔ አበባ ሕዋዬን በመዓዛዋ ብታውደውም እኔ መደሰቱን አላወቅሁበትም። ስለ ጥፍሮች ያወራችው ወሬ የመሳሳት ስሜት ሊያሳድርብኝ ሲገባው እንዲያውም አበሳጭቶኝ ነበር ...» ብሎ አንድ ቀን ምስጢሩን አካፍሎኛል።

ከዚሁ ጋር በማያያዝ የሆዱን አውጥቶ ነገረኝ፣

«ያን ጊዜ ምንም ሊገባኝ አልቻለም እንጂ! እሷን መገመት የነበረብኝ በንግግሯ ሳይሆን በተግባሯ ነበር። በመዓዛዋ እያወደች ብርሃን ትፈነጥቅልኝ ነበር። መኩብለል አልነበረብኝም። ከሞኝ ብልጣ ብልጥነት ጀርባ የባሕሪዋን አዛኝነት ማወቅ ነበረብኝ። ያበቦች ጠባይ አቤት የቅራኔው ብዛት! ልጅ ስለ ነበርኩ መውደዱን አላወቅሁበትም።



፱

ለመኰብለል በዱር አእዋፍ የፍልሰት በረራ የተጠቀመ ይመስላል። የጒዞው ዕለት በጧት ተነሥቶ ሕዋውን በሚገባ አስተካከለ። ያልጠፉትን እሳተ ገሞራዎች ጭስ ማውጫ በጥ ንቃቄ አጸዳ። ያልጠፉ እሳተ ገሞራዎች ሁለት ነበሩት። የነሱ መኖር ጧት ጧት ቁርስ ለማሞቅ በጣም ምቹ ነው። አንድ የጠፋ እሳተ ገሞራም ነበረው። እሱ እንደሚለው «መቼም አይታወቅና» ያንንም ከንፈሩን ጠራረገው። መተንፈሻቸው በንጹሕ ከተያዘ እሳተ ገሞራዎች ቀስ እያሉ በሥርዓት ይንበለበላሉ እንጂ አይፈነዱም። የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ እንደ ምድጃ እሳት ነው። በርግጥ እኛ አምንኖርባት ምድራዊት ዓለም ላይ መጠናችን በጣም አነስተኛ ስለሆነ እሳተ ገሞራዎቹን ለማጽዳት ይሳነናል። ብዙ ችግር የሚያመጡብንም በዚሁ ምክንያት ነው።

ታዳጊው ልዑል ትንሽ እየተከዘ የቀሩትን የወርካ ችግኞች ነቀላቸው። ተመልሶ መምጣት የሌለበት መስሎት ነው። ያን ዕለት ጧት ግን የወትሮ ተግባሩን ሁሉ ያከናወነው በጣም ደስ እያለው ነው። አበባዋን ለመጨረሻ ጊዜ ውኃ አጠጥቶ ክዳኑን ሊያደርግላት ሲል እንባ እንባ እንዳለው ተሰማው።

- ደኅና ሁኚ አላት አበባዋን።
- አሷ ግን አልመለሰችለትም።
- አሁንም ደኅና ሁኚ አላት።
- አበባዋ ላል አሳላት። ግን በያዛት ጒንፋን ምክንያት እልነበረም።
- መጨረሻ «ቀብጬ ነበር» አለችው። «ይቅርታ አድርግልኝ፤ ደስተኛ ለመሆን ሞክር።»

ሳትወቅሰው መቅረቷ ገረመው። ግራ ገብቶት ክዳኑን ወደ ላይ ገልብጦ አንደ ያዘ ቆሞ ቀረ። የረጋ ለስላሳነቷ ሊገባው አልቻለም።



ያልጠፉትን እሳተ ገሞራዎች ሟስ ማውጫ
በጥንቃቄ አጸዳ።

- አዎ እወድሃለሁ እኮ አለችው አበባይቱ። ሳታውቀው የቀረኸው በኔ ጥፋት ነው። ግድ የለም አንተም ብትሆን እንደኔ ቀብጠህ ነበር። ይኸን ክዳን ወዲያ በለው። ካሁን ወዲያ አልፈልገውም።

- ነፋሱሳ?

- የያዘኝ ጉንፋን ይኸንን ያህል አይደለም። የሌሊቱ ቀዝቃዛ አየር ለጤናዬ ጥሩ ነው። አበባ አይደለሁም።

- እውሬዎቹሳ?

- ቢራቢሮዎች ምን እንደሚመስሉ ማወቅ ከፈለግሁ አንድ ሁለት ቅምቡርሶች በትእግሥት መቀበል መቻል ይኖርብኛል። ቢራቢሮዎች በጣም ያምራሉ ይባላል። ሌላማ ማ ይጠይቀኛል? አንተም እሩቅ አገር መሄድህ ነው። ትልልቆቹን አራዊት እንደ ሆነ ምንም አልፈራ። ጥፍሮች አሉኝ። እንደ ሞኝ አራት እሾኮቿን አሳየችኝ። ከዚያም፣

- አትንቀርፈፍብኝ ያበሽቃል። እሄዳለሁ ብለሃል። ሂድ ወዲያ።

ይኸ ሁሉ ስታለቅስ እንዳላያት ነው። ኩራተኛነቷ ይኸ ነው የማይባል አበባ ነበረች...።

I

ታዳጊው ልዑል የሚገኘው በቁጥር 325፣ 326፣ 327፣ 328፣ 329፣ እና 330 ሕዋ አካላት አካባቢ ነበር። ሥራ እንዳይፈታና ትምህርትም እንዲሆነው ይጐበኛቸው ጀመረ። የመጀመሪያው ሕዋ የንጉሥ መኖሪያ ነበር። ንጉሡ በሙጭልጭላ ለምድ የተጌጠ ቀይ የድሃ ካባ ለብሶ ጌጥ በማይበዛበት ዙፋን ላይ በግርማ ሞገስ ተቀምጧል።

- ንጉሡ ታዳጊውን ልዑል ሲያይ ድምፁን ከፍ አደረገና፣ «ጎሽ! አንድ ዜጋ ተገኘ» አለ።

ታዳጊው ልዑልም፣

- ከዚህ ቀደም ሳያየኝ አሁን እንዴት ሊያውቀኝ ቻለ? ብሎ ገረመው:: ለነገሥታት ዓለም ቀላል ሆና እንደምትታያቸው አያውቅም ነበር:: ለነሱ ሰው ሁሉ ዜጋቸው ነው::

- አንጋሽ በማግኘቱ ተኮራርቶ የነበረው ንጉሥ፣ «እስቲ ቀረብ በል ልይህ» አለው::

ታዳጊው ልዑል የሚቀመጥበት ቦታ ባይኑ ቢፈልግ አጣ፣ በንጉሡ ባለ ሙጭልጭላ ካባ ሕዋው ተጣቦ ነበር:: ቆሞ ቀረና ደክሞት ስለ ነበረ አዛጋው::

- እንጉሥ ፊት ማዛጋት ሥነ ሥርዓት መጣስ ነው:: እንዳይደግምህ፣ አለው ንጉሡ::

- ታዳጊው ልዑል አፍሮ፣ «አቅቶኝ ነው፣ ጉዞዬ ረዥም ስለ ነበረ እንቅልፍ አላገኘሁም... ብሎ መልስ ሰጠ::

- እንደዚህ ከሆነ አዛጋ አለው ንጉሡ:: ሰው ሲያዛጋ ካየሁ ብዙ ዓመት ሆኖኛል:: ሲያዛጉ ማየት ብርቅ ሆኖብኛል:: በል አሁንም አዛጋ:: ትእዛዝ ነው::


- ፍራት ፍራት ይለኛል... አልቻልኩም... አለ ታዳጊው ልዑል ፊቱ ቀይ እየሆነ::

- ነው እንዴ! ነው እንዴ! አለ ንጉሡ:: እንግዲያው አንዳንድ ጊዜ አዛጋ፣ አንዳንድ ጊዜ...::

ትንሽ ያልጐመጉማል፣ የተቀየመም ይመስል ነበር::

ንጉሡ ከሁሉ ይበልጥ የሚፈልገው ሥልጣኑ እንዲከበርለት ነው:: እምቢ ማለትን አይቀበልም:: አምባገነን ንጉሥ ነው:: ነገር ግን ደግ ስለ ነበረ የሚሰጠው ትእዛዝ አግባብ ያለው ነበር:: ንጉሡ እየደጋገመ የሚናገረው አንድ አባባል ነበረው፣ ይኸውም «አንዱን የጦር መሪ የባሕር ወፍ ሁን የሚል ትእዛዝ ሰጥቼው ትእዛዜን ሳይፈጽም ቢቀር እሱ ጥፋት የለበትም:: ጥፋቱ የኔ ነው» የሚል ነው::

- ታዳጊው ልዑል እየፈራ እየቸረ፣ «መቀመጥ ይፈቀድልኛል?» አለ::



- ንጉሡ የባለሙጭልጭላ ካባውን ዘርፍ ሰብሰብ አደረገና በታላቅ ግርማ፣ እንድትቀመጥ አዝዤሃለሁ አለው።

ታዳጊው ልዑል ግን እየተገረመ ነው። ሕዋው በጣም አነስተኛ፣ ንጉሡ የሚነግሠው እምን ላይ ነው?

- ግርማዊ ሆይ አለ ታዳጊው ልዑል... ጥያቄ ሳቀርብልዎ ከይቅርታ ጋራ ነው...።

- ንጉሡ ወዲያው ቀበል አድርጎ እንድትጠይቅ ታዘሃል አለው::
- ግርማዊ ሆይ... የምን ንጉሥ ነዎ?
- የሁሉም አለ ንጉሡ በቀላል አባባል::
- የሁሉም?
- ንጉሡ የተቀመጠበትን ሕዋ፣ ሌሎቹን ሕዋ አካላትና ከዋክብቶቹን በተቆጠበ የእጅ ምልክት አሳየው::
- የዚህ ሁሉ?... አለ ታዳጊው ልዑል::
- የዚህ ሁሉ... ብሎ መለሰለት ንጉሡ::

ይኸ ንጉሥ አንባገነናዊ ብቻ ሳይሆን ሁለንተናዊም ንጉሥ ነው::

- ከዋክብቱ ይታዘዙልዎታል?
- እንዴ! አለ ንጉሡ:: ወዲያው ነው የሚታዘዙልኝ፣ ሥርዓት አልባነት እኔ ዘንድ ተቀባይነት የለውም::

ይህን የመሰለው ሥልጣን ታዳጊውን ልዑል አድናቆት አሳደረበት:: ይህን ሥልጣን የያዘው እሱ ቢሆን ኖሮ በቀን አርባ አራት ሳይሆን ሰባ ሁለት ብሎም መቶ ወይም ሁለት መቶ ጊዜ ወንበሩን ሳያነቃንቅ ጀንበር ስትጠልቅ ለማየት በቻለም ነበር!

ጥሏት የመጣው ሕዋ ትዝ አያለችው ትንሽ ያዝን ስለ ነበረ እንደምንም ብሎ ተደፋፈረና ንጉሡ አንዲት ነገር እንዲፈቅድለት ጠየቀው፣

- ፀሐይ ስትጠልቅ ማየት እፈልጋለሁ... ደስ እንዲለኝ... ፀሐይቱን እንድትጠልቅ ይዘሂት...::
- አንዱን የጦር መሪ እንደ ቢራቢሮ ከአበባ ወደ አበባ እንዲበርር ወይም አስጨናቂ ተውኔት እንዲጽፍ ወይም ደግሞ ወደ ባሕር ወፍ እንዲለወጥ ትእዛዝ ብሰጠውና የታዘዘውን ሳይፈጽም ቢቀር ከእኔና ከርሱ ጥፋተኛው ማን ሊሆን ነው?
- ታዳጊው ልዑል ቀጭጥ አድርጎ፣ እርስዎ ነዎት አለው::
- ትክክል:: ከእያንዳንዱ መጠየቅ የሚገባው ሊሰጥ የሚችለውን ብቻ ነው፣ አለ ንጉሡ ሲመልስለት:: የሥልጣን ዋና መሠረቱ

አግባብነት ነው:: ሕዝብህን ባሕር ዘለህ ግባ ብለህ ብታዘው አብዮት ያስነሣል:: ትእዛዜን የማስከበር መብት የሚሰጠኝ የትእዛዞቼ ተገቢነት ነው::

አንድ ጊዜ ያቀረበውን ጥያቄ ፈጽሞ የማይዘነጋው ታዳጊ ልዑል፣ «ታዲያ የኔ የፀሐይቱ መጥለቅ ጉዳይ እንዴት ሊሆን ነው?» ብሎ አስታወሰ::

- ፀሐይቱ ትጠልቅልሃለች:: አስገድዳታለሁ:: ባስተዳደር ጥበቤ ግን ሁኔታው አመቺ እስኪሆን ድረስ እጠብቃለሁ::

- መቼ ነው? ብሎ ጠየቀ ታዳጊው ልዑል::

- አስቲ ! አስቲ ! ወደ... ወደ... ዛሬማ ወደ አንድ ሰዓት ከአርባ ላይ ትጠልቃለች! እንዴት አድርጋ ትእዛዜን እንደምታከብር ቆይ ታያለህ::

ታዳጊው ልዑል አዛጋው:: የፀሐይቱ መጥለቅ ስላመለጠው ቅር ብሎታል:: በዚህ ላይ ትንሽ እንደ መሰልቸትም ብሎታልና::

- ንጉሡን እዚህ የሚያቆየኝ ምንም ጉዳይ የለኝም:: እንግዲህ ተመልሼ ልሂድ አለው::

- አንድ ዜጋ ስላገኘ ተደስቶ የነበረው ንጉሥ አትሂድ ብሎ መለመለት:: አትሂድ ሚኒስትር አደርግሃለሁ!

- የምን ሚኒስትር?

- የ ... ፍትሕ!

- ተፋራጅ የለም!

- አይታወቅም አለው ንጉሥ:: መንግሥቴን ገና ተዘዋውሬ አልጐበኘሁም:: ዕድሜ ተጭኖኛል፣ ሠረገላ ለማስገባት ቦታ ይጠበኛል፣ በእግሬ እንዳልሄድ ይደክመኛል::

- አዎ! አለ ታዳጊው ልዑል ከሕዋ አካሉ ባሻገር ያለውን መልሶ ለማየት ጉንበስ አለና፣ አይቼዋለሁኮ:: በዚያም በኩል ማንም የለ::...::

- ራስህ በራስህ ትፈርዳለሃ አለው ንጉሡ:: በጣም አስቸጋሪ ሙያ ነው:: በሰው ከመፍረድ በራስ መፍረድ ይከብዳል:: በራስህ

ላይ ትክክለኛ ፍርድ መስጠት ከቻልክ በእውነቱ ብልህ ነህ ማለት ነው::

- እኔ የትም ቢሆን ራሴን በራሴ መፍረድ እችላለሁ:: እዚህ መኖር አያስፈልገኝም::

- እስቲ! እስቲ ! አለ ንጉሡ፣ እኔ ሕዋ ውስጥ አንዱ ሥርቻ አንድ አሮጌ ዓይጥ ያለ ይመስለኛል:: ሌሊት እስማዋለሁ ያንን አሮጌ ዓይጥ ልትዳኘው ትችላለህ:: አልፎ አልፎ የሞት ፍርድ ልትፈርድበት ትችላለህ:: ይኸንን ካደረግህ ሕይወቱ ያንተ ፍርድ ተገዢ ይሆናል ማለት ነው:: አንተ ግን ሕይወቱን ለመቆጠብ ሞት በተፈረደበት ቀኖጥር በምሕረት ታልፈዋለህ:: ያለው አንድ እሱ ብቻ ነው::

- እኔ የሞት ፍርድ መወሰን አልወድም፤ መሄዴ ነው አለ ታዳጊው ልዑል::

- አይሆንም አለ ንጉሡ::

ታዳጊው ልዑል ግን ጓዙን አዘጋጅቶ ጨርሶ ስለ ነበረ አዛውንቱን ንጉሥ ማስቀየም ስላልፈለገ እንዲህ አለው፤

- የግርማዊነትዎን ትእዛዝ በትክክል እንዳከብር ከፈቀዱ የሚሰጡኝ ትእዛዝ አግባብ ያለው ይሁን:: ለምሳሌ ግርማዊነትዎ በአንድ ደቂቃ ውስጥ እንድሄድ ሊያዘኝ ይችላል:: ሁኔታው አመቺ ይመስለኛል...::

- ንጉሡ ምንም ስላልመለሱለት ታዳጊው ልዑል በፊት ትንሽ አመነና ከዚያ እየጨነቀው ጉዞውን ጀመረ::

- ንጉሡ ቶሎ አለና ድምፁን ከፍ አድርጎ መልእክተኛዬ አድርጌሃለሁ አለው::

አባባሉ ልክ ከፍተኛ ሥልጣን እንዳለው ነው::

ታዳጊው ልዑል በልቡ እነዚህ ትልልቅ ሰዎች ይገርማሉ እያለ ጉዞውን ቀጠለ::

፲፩

ሁለተኛው የሕዋ አካል ላይ የሚኖረው አንድ ጉረኛ ሰው ነበር።

- ጉረኛው ሰው ታዳጊውን ልዑል ገና ከሩቅ ሲያየው እሰይ! እሰይ! አድናቂ ሊጐበኝ መጣ አለ።



ለጉረኞች ሌሎቹ ሰዎች ሁሉ አድናቂዎች ናቸው።

- ጤና ይስጥልኝ አለ ታዳጊው ልዑል። ባርኔጣዎ ያሥቃል።

- ሠላም መስጫ ነው፤ ብሎ መለሰለት ጉረኛው። ሆነ ብለው ሲያደንቁኝ እጅ ለመንሣት የማወልቀው ነው። የሚያሳዝነው ነገር በዚህ በኩል ማንም አያልፍም።

- ታዳጊው ልዑል ምንም ስላልገባው «ነው እንዴ?» አለ።

- ውስጥ እጆችህን አማታ ብሎ መከረው ጉረኛው።

- ታዳጊው ልዑል እጆቹን አማታ።



ጕረኛው በትሕትና ባርኔጣውን አውልቆ እጅ ነሣ።

ታዳጊው ልዑል በሆዱ ይኸ ደግሞ ከንጉሡ ጕብኝት የበለጠ አስቂኝ ጕብኝት ነው አለ። ውስጥ እጆቹን በድጋሚ አማታ። ጕረኛውም እንደገና ባርኔጣውን እያወለቀ እጅ መንሣት ጀመረ። ልምምዱ ሲደጋገምበት ጊዜ ታዳጊው ልዑል ጨዋታው በአምስት ደቂቃ ውስጥ ሰለቸውና፣

- ባርኔጣው እንዲወድቅ ምንድነው የሚደረገው? ብሎ ጠየቀው።

ጕረኛው ግን አላዳመጠውም። ጕረኞች መቼውንም ቢሆን ጆሮ የሚሰጡት ለምስጋና ብቻ ነው።

- ለመሆኑ በጣም ታደንቀኛለህ? ብሎ ታዳጊውን ልዑል ጠየቀው።

- ማድነቅ ማለት ትርጉሙ ምንድነው?

- ማድነቅ ማለት በዚህ ሕዋ አካል ውስጥ በመልኬ በአለባበሴ በሀብቴና በእውቀቴ ከማንም እንደምበልጥ መቀበል ማለት ነው::

- ሕዋው ላይኮ ያለኸው አንተ ብቻ ነህ!

- እስቲ አስደስተኝ:: ያም ሆኖ አድንቀኝ::

- ታዳጊው ልዑል በአሉታ መልክ ትከሻውን በመጠኑ ወደ ላይ ከፍ አደረገና «ለመሆኑ አድናቆት ምን ይደርግልሃል?» አለው::

ከዚያም ታዳጊው ልዑል ተነሥቶ ሄደ::

በጉዞ ላይ ሳለ፣ ትልልቆቹ ሰዎች በእውነቱ ነገራቸው ሁሉ ግራ የሚያጋባ ነው እያለ በሆዱ አሰበ::

፲፪

የሚቀጥለው ሕዋ አካል ነዋሪ አንድ ጠጪ ሰው ነበር:: ጉብኝቱ በጣም አጭር ቢሆንም ታዳጊው ልዑል ከታላቅ ትካዜ ውስጥ ገባ::

- በባዶ ጠርሙስና በሙሉ ጠርሙስ ክምችት መካከል በዝምታ ቁጭ ብሎ የነበረውን ጠጪ፣ «ምን እያደረግህ ነው?» ብሎ ቢጠይቀው::

- ጠጪው እየደበተው «እጠጣለሁ» ብሎ መለሰለት::

- ለምን ትጠጣለህ? ቢለው፣

- ለመርሳት አለ ጠጪው::

- ገና ሲያየው አዝኖለት የነበረው ታዳጊ ልዑል፣ «ምን ለመርሳት?» ሲል ጥያቄውን ቀጠለ::

- ጠጪው አቀረቀረና፣ «ሐፍረቴን ለመርሳት» ብሎ እውነቱን ነገረው::

- ታዳጊው ልዑል ሊረዳው ስለ ፊለገ «የሚያሳፍርህ ምንድነው?» ብሎ ለማወቅ ሞከረ::

- የመጠጣት ሐፍረት! አለና ከዚያ በኋላ ፊጽሞ ጸጥ አለ::

ታዳጊው ልዑልም ሐሳብ ገብቶት ተነሥቶ ሄደ::

በጐዘው ላይ ትልልቆቹ ሰዎች እውነትም ነገራቸው ሁሉ እጅግ በጣም ግራ የሚያጋባ ነው እያለ በሆዱ አሰበ::

፲፫

አራተኛው የሕዋ አካል የነጋዴው ነበር:: በሥራ ከመወጠሩ የተነሣ ታዳጊው ልዑል ሲደርስ ቀና ብሎ እንኳን አላየውም::

- ጤና ይስጥልኝ አለው ልዑሉ:: ሲጃራዎ ጠፍቷል::

- ሦስት ሲደመር ሁለት ይሆናል አምስት:: አምስትና ሰባት አሥራ ሁለት:: አሥራ አምስት ሲደመር ሰባት ሃያ ሁለት:: በሃያ ሁለት ላይ ስድስት ሲጨመር ሃያ ስምንት:: ሲጃራውን መልሶ ለማቀጣጠል ጊዜ የለም:: ሃያ ስድስት ሲደመር አምስት ሠላሳ አንድ:: ስለዚህ አምስት መቶ አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሠላሳ አንድ ነው::

- አምስት መቶ ሚሊዮን ምን?

- እንዴ! አሁንም እዚሁ ነህ? አምስት መቶ አንድ ሚሊዮን ... ምን እንደሆነ ጠፋኝ ... ብዙ ሥራ አለኝ! እኔ ፍሬ ባለው ነገር ነው እንጂ እንዳንተ ጊዜዬን በዋዛ ፈዛዛ አላሳልፍም! ሁለት ሲደመር አምስት ይሆናል ሰባት ...

- አንድ ጊዜ ጥያቄ ካቀረበ ቢሞት የማይለቀው ታዳጊ ልዑል አሁንም፣ «አምስት መቶ ሚሊዮን ምን ብሎ» በድጋሚ ጠየቀው::



ነጋዴው ቀና ብሎ፣

- እዚህ ሕዋ አካል ላይ ሃምሳ አራት ዓመት ስኖር ሰው ያሰቸገረኝ ሦስት ጊዜ ብቻ ነው። የመጀመያሪው የዛሬ ሃያ ሁለት ዓመት አንድ ከየት እንደ መጣ የማይታወቅ ጥንዚዛ። ጥዝ ጥዝ በሚል አስከፊ ድምፁ ምክንያት አንድ ድምር ላይ አራት ጊዜ ተሳሳትኩ። ሁለተኛው ከአሥራ አንድ ዓመት በፊት የመጣብኝ ቀላርጥማት ነው። የአካል እንቅስቃሴ ያንሰኛል። ለመንከራፈፍ

ጊዜ የለኝም። እኔ ቁም ነገረኛ ሰው ነኝ። ሦስተኛው ... ይኸው እንግዲህ! የት ላይ ነበርኩ አምስት መቶ አንድ ሚሊዮን ...

- ሚሊዮን ምን?

ነጋዴው በሰላም ለመገላገል ተስፋ እንደ ሌለው ገባው፣

- አንድ ሚሊዮን አንዳንድ ጊዜ ሰማይ ላይ የሚታዩት እነዚያ ጥቃቅን ነገሮች።

- ዝንቦች?

- የለም የሚያብለጨልጩ ጥቃቅን ነገሮች።

- ንቦች?

- አይደለም። ሰነፍችን ሰመመን የሚያስይዙ ጥቃቅን ወርቅማ ነገሮች። እኔኮ ቀልድ አላውቅም! ለሰመመን ጊዜ የለኝም።

- አሃ! ኮከቦች ማለትህ ነው?

- በትክክል። ኮከቦች።

- አምስት መቶ ሚሊዮን ኮከቦች ምን ያደርጉልሃል?

- አምስት መቶ አንድ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሠላሳ አንድ። እኔ ዘንድ ቀልድ የለም ጠንቃቃ ነኝ።

- እነዚህ ኮከቦች ምን ያደርጉልሃል?

- እሚያደርጉልኝ?

- እ!

- ምንም። ንብረቶቼ ናቸው።

- ኮከቦች ያንተ ንብረቶች ናቸው?

- አዎ።

- ከዚህ ቀደም ያየሁት ሌላ ንጉሥ እሱም...።

- ነገሥታት ንብረት የላቸውም። እነሱ አልጋ ይዘው መንገሥ ነው። በጣም የተለየ ነገር ነው።

- የከዋክብት ባለንብረት መሆን ምን ያደርግልሃል?

- ሀብታም ለመሆን ይጠቅመኛል።

- ሀብታም መሆንስ ምን ያደርግልሃል?

- ከተገኙ ሌሎች ኮከቦች ለመግዛት።

ታዳጊው ልዑል በልቡ ይኸኛውም ሰውዬ አስተሳሰቡ ከሞላ ጐደል ከሰካራሙ ጋር ተመሳሳይ ነው አለ::

ያም ሆኖ ጥያቄዎቹን በመቀጠል፣

- የኮከቦች ባለንብረት ለመሆን እንዴት ነው የሚቻለው?

ነጋዴው እየተነጫነጨ «የማናቸው?» ብሎ ጥያቄውን በጥያቄ መለሰለት::

- ምን እውቄ:: የማንም አይደሉ::

- ይኸ ከሆነ የኔ ናቸው፣ ምክንያቱም መጀመሪያ ያሰብኩበት እኔ ነኝ::

- ይበቃል?

- እንዴ! ባለቤት የሌለው አልማዝ ሲገኝ የራስህ ታደርገዋለህ:: ባለቤት የሌለው ደሴት ሲገኝ የራስህ ይሆናል:: ከሰው ቀድመህ:: እንድ ሐሳብ ቢመጣልህ የባለቤትነት ማረጋገጫ ታወጣና የራስህ ግኝት ይሆናል:: እኔም የከዋክብቱ ባለንብረት የሆንኩት ከኔ በፊት ማንም አስቦበት ስላልነበረ ነው::

- እውነትህን ነው አለ ታዳጊው ልዑል:: ምን ታደርጋቸዋለህ?

- አስተዳድራቸዋለሁ፣ እየደጋገምኩ እቈጥራቸዋለሁ አለ:: ነጋዴው አስቸጋሪ ነው:: እኔ ግን ቀልድ አላውቅም!

ታዳጊው ልዑል እሁንም ቢሆን ነገሩ አላረካውም::

- እኔ ያንገት ልብስ ካለኝ ጠምጥሜው ለመሄድ እችላለሁ:: እኔ አንድ አበባ ቢኖረኝ አበባዬን ቀጥፌ ለመውሰድ እችላለሁ:: አንተ ግን ከዋክብቱን መልቀም አትችልም!

- የለም! ግን ባንክ ቤት በወለድ ላስመዘግባቸው እችላለሁ::

- ምን ማለት ነው?

- የኮከቦቼን ቁጥር አንድ ብጣሽ ወረቀት ላይ እጽፋለሁ ማለት ነው:: ከዚያም ወረቀቱን መሳቢያ ውስጥ እቆልፍበታለሁ::

- በቃ ይኸው ነው?

- በቃ!

- ትንሹ ልዑል በሃሳቡ፣ «ያሥቃል» አለ:: በመጠኑ ልብ ይነካል:: ግን የምር የሚሆን አይመስልም::

ታዳጊው ልዑል ስለ ቁም ነገር ያለው አስተሳሰብ ከትልልቆቹ ሰዎች አስተሳሰብ እጅግ የተለየ ነው።

- እኔ አለ ታዳጊው ልዑል ንግግሩን በመቀጠል ሁልቀን ውኃ የማጠጣት አበባ አለችኝ። በየሳምንቱ የማጸዳቸው ሦስት እሳተ ገሞራዎች አሉኝ። ሦስት የሆኑት የጠፋውንም ጭምር ስለማጸዳው ነው። ማን ያውቃል። እሳተ ገሞራዎቹም ሆኑ አበባይቱ የኔ ንብረቶች መሆናቸው ይበጃቸዋል። እንተ ግን ኮከቦቹን አትጠቅማቸውም...። ነጋዴው የሚመልሰው ስላጣ አፉን ከፍቶ ቀረ፣ ታዳጊውም ልዑል ጥሎት ሄደ።

በጉዞው ላይ እንዲያው ዝም ብሎ ትልልቆቹ ሰዎች በእውነቱ ይደንቃሉ እያለ በሆዱ ያስብ ነበር።

፲፩

እምስተኛው የሕዋ አካል ዕጹብ ድንቅ ነበር። ከሁሉም ያንሳል። ያለው ቦታ አንድ የጐዳና መብራትና እንድ መብራት አብሪ ብቻ የሚያስገባ ነው። እሰማይ ላይ፣ ቤትም ሕዝብም በሌለበት ሕዋ አካል ላይ አንድ መብራትና አንድ አብሪ ለምን እንደሚጠቅሙ ታዳጊው ልዑል ሊገባው አልቻለም። በሐሳቡ ግን፣

- ይኸ ሰው ምናልባት ግራ ተጋብቶ ይሆናል። ነገር ግን ግራቢስነቱ ከንጉሡም ከጐረኛውም ከነጋዴውም ከጠጪውም ያነስ ነው። ባይሆን እንኳ የሱ ሥራ ትርጉም አለው። መብራቱን ሲለኩስ አንድ ኮከብ ወይም አንድ እበባ እንደ ተወለደ ይቈጠራል። መብራቱን ሲያጠፋም እበባይቱ ወይም ኮከቧ እንቅልፋቸው ይመጣል ማለት ነው። በጣም ደስ የሚል ሥራ ነው። ደስ የሚል ከሆነ ዘንድ በውነቱ ጠቃሚ ነው።

ሕዋ አካሉ ላይ እንዳረፈ መብራት አብሪውን በአክብሮት እጅ ነሣ፣

- ጤና ይስጥልኝ፣ መብራትህን ምነው አሁን አጠፋኸው?

- መመሪያው ምን ያዛል? ብሎ መለሰለት አብሪው። ሥራዬ መብራቱን ማጥፋት ደኅና አምሽ።

መልሶ አበራው።

- ምነው መልሰህ አበራኸው?

- መመሪያው ያዛል። ብሎ መለሰ መብራት አብሪው።

- አልገባኝም አለ።

- ገባኝ አልገባኝ ብሎ ነገር የለም። መመሪያ መመሪያ ነው። ጤና ይስጥልኝ።

ከዚያም መብራቱን አጠፋው።

ቀጥሎም ባለ ቀይ መሥመር መሐረቡን አውጥቶ የግንባሩን ላብ ጠረገ።

- ይኸ የኔ ሙያ በጣም ከባድ ነው። ዱሮ ጥሩ ነበር። ሚት አጥፍቼ ማታ አበራለሁ። በተረፈ ቀኑን ሙሉ ማረፍ፣ ሲመሽ መተኛት ነበር።

- ከዚያ ወዲህ መመሪያው ተለወጠ?

- መመሪያው አልተለወጠም፣ አለ መብራት አብሪው። ይኸ ነው የሚያሳዝነው። ከዓመት ዓመት የሕዋ አካሉ የመሽከርከር ፍጥነት ሲጨምረ መመሪያው ግን አልተለወጠም!

- ታዲያ ምን በጀህ? አለ ታዳጊው ልዑል።

- አሁንማ በደቂቃ አንድ ዙር ስትሽከረከር አንዲት ሰከንድ እንኳን ፋታ የለኝም። በየደቂቃው ማብራት ማጥፋት ብቻ ነው!

- ያሥቃል! አንተ አገር የቀኑ ርዝመት አንድ ደቂቃ ብቻ ነው!

- ምንም አያሥቅ አለ መብራት አብሪው፤ መነጋገር ከጀመርን ይኸው አንድ ወር ሆኖናል።

- አንድ ወር?

- አዎ፣ ሠላሳ ደቂቃ ሠላሳ ቀን! ደህና እደር።

ብሎም መብራቱን መልሶ ለኰሰ።



ይኸ የኔ ሙያ በጣም ክብድ ነው።

ታዳጊው ልዑልም ይኸንን መመሪያውን በጥብቅ አክብሮ የሚኖር መብራት አብሪ አስተዋለና ወደደው:: ድሮ ራሱ ወንበሩን እያን቏ቀቀ ለማየት ይፈልገው የነበረው የጀንበር መጥለቅ ትዝ አለው:: ወዳጁን መርዳት ፈለገና፣

.. - ታውቃለህ... በፈለግህ ጊዜ ማረፍ የሚያስችልህ ዘዴ አውቃለሁ...::

- የት ተገኝቶ! አለ መብራት አብሪው::

ምክንያቱም አንዱ ሰው ታማኝም ሰነፍም ሊሆን ይችላል::

ታዳጊው ልዑል ቀጥሎ፣

- ሕዋው ከማነሱ የተነሣ በሦስት እርምጃ ትዞረዋለህ:: ሁልጊዜ እፀሐይ ላይ ለመሆን ዝግ ብለህ መራመድ ብቻ ነው:: ማረፍ ሲያምርህ መራመድ... በዚህ ዓይነት ቀኑን እንደ ፈቀደህ ታራዝመዋለህ::

- ይኸ የትም አያደርሰኝ፣ አለ መብራት አብሪው:: እኔ በሕይወቴ የምወደው እንቅልፍ ነው::

- ወይ አለመታደል አለው ታዳጊው ልዑል::

ከዚያም መብራቱን አጠፋው::

ታዳጊው ልዑል መንገዱን ወደፊት ሲቀጥል ይኸንን ሰው ንጉሡም ጉረኛውም ጠጪውም ነጋዴውም ይንቁት ይሆናል:: እኔ ግን ሊሥቁበት የማይገባው እሱ ብቻ ይመስለኛል:: ምናልባት እሱ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለሌላም ነገር ስለሚጨነቅ ይሆናል::

እያዘነ እህህ አለና፣

ቢሆንማ ወዳጅ የማደርገው እሱን ብቻ ነበር:: ግን ምን ያደርጋል ያለበት ሕዋ አካል በእውነቱ በጣም ጠባብ ነው:: ለሁለት ሰው አይበቃም:: ...

ታዳጊው ልዑል ደፍሮ ባይገልጸውም በይበልጥ ይከነክነው የነበረው ያ ዕድለኛ ሕዋ አካል በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ጀንበሯ ሺህ አራት መቶ አርባ ጊዜ ስለምትጠልቅ ነው!

፲፫

ስድስተኛው ሕዋ አካል አሥር ጊዜ ይሰፋል። እጅግ በጣም ትላልቅ መጻሕፍት የሚጽፉ አዛውንት ሰው መኖሪያ ነው።

- ታዳጊውን ልዑል ሲያዩ «ወይ ጉድ! አገር አሳሽ» አሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው።

ታዳጊው ልዑል እጠረጴዛው ላይ ተቀመጠና አንድ አፍታ እፎይ አለ። እስካሁንም ጉዞ በዝቶበታል።

- ከየት ነው የምትመጣው? አሉት አዛውንቱ።

- ይኸ ወፍራም መጽሐፍ ምንድነው? አላቸው ታዳጊው ልዑል። እዚህ ምን ያደርጋሉ?

- የገጸ ምድር ባለሙያ ነኝ አሉት አዛውንቱ።

- የገጸ ምድር ባለሙያ ምንድነው?

- እሱማ ባሕሮች፣ ወንዞች፣ ከተማዎች፣ ተራራዎች፣ በረሃዎች የሚገኙበትን ቦታ የሚያውቅ ሊቅ ነው።

- ይኸ በእውነቱ ትኩረት የሚጋብዝ ነገር ነው፣ አለ ታዳጊው ልዑል። ሙያ ማለት ይኸ ነው አለና የገጸ ምድር ባለሙያውን ሕዋ አካል በዓይኑ ቃኘ። ይኸን የመሰለ ግርማ ያለው ሕዋ እስከ ዛሬ ገጥሞት አያውቅም።

- የርስዎ ሕዋ በጣም ያምራል። ውቅያኖሶች አሉበት?

- እኔ ምን አውቄ አሉ የገጸ ምድሩ አዋቂ።

- እንዴ! (ታዳጊው ልዑል ቅር ተሰኝቷል)። ተራራዎችስ?

- እኔ ምን አውቄ አሉ የገጸ ምድሩ አዋቂ።

- ከተማዎች፣ ወንዞች፣ በረሃዎችሳ?

- እነሱንም በፍጹም አላውቅም አሉ የገጸ ምድር አዋቂው።



- የገጸ ምድር ሊቅ እኮ ነዎት!

- ልክ ነው። አሉ አዋቂው፣ ነገር ግን አገር አሳሽ አይደለሁም። የአገር አሳሾች እጥረት አለብኝ። እየዞረ ከተሞች ወንዞች ተራራዎች ባሕሮች ውቅያኖሶች በረሃዎች የሚቈጥረው የገጸ ምድር አዋቂ አይደለም። የገጸ ምድር አዋቂ ታላቅ ሰው ስለሆነ ለዙረት ጊዜ የለውም። ከጽሕፈት ቤቱ አይወጣም። ግን አገር አሳሾችን አየተቀበለ ያነጋግራል። እየመረመረ ትውስታቸውን ይመዘግባል። ከነሱ መካከል ያንዱ ትዝታ ጠቃሚ ሲመስለው የገጸ ምድሩ ሊቅ የግለሰቡን ሥነ ምግባር ያስመረምራል።

- ምክንያቱ ምንድነው?

- አንድ አገር አሳሽ ሐሰተኛ ነገር የተናገረ እንደሆነ በገጸ ምድር መጻሕፍት ላይ የሚያስከትለው አደጋ ከፍተኛ ነው። መጠጥ የሚያበዛም አገር አሳሽ ያው ነው።

- ለምን አለ ታዳጊው ልዑል።

- ሰካራሞች ነገሩ ሁሉ እጥፍ እየሆነ ስለሚታያቸው ነው። ስለሆነም የገጸ ምድሩ ባለሙያ አንድ ተራራ ብቻ ያለበትን ቦታ ሁለት ተራራዎች ብሎ ይመዘግባል።

- አገር አሳሽ የሆነ ብቃት የሌለው አንድ ግለሰብ አውቃለሁ።

- ይሆናል። እንግዲህ የአሳሹ ሥነ ምግባር ጥሩ መሆኑ ሲታመንበት ስለ ግኝቱ ይመረመራል።

- እቦታው ድረስ ተሂዶ ይታያል?

- የለም። ያማ ነገሩን በጣም ውስብስብ ያደርገዋል። አገር አሳሹ ማስረጃ እንዲያቀርብ ይገደዳል። ለምሳሌ ግኝቱ የሚመለከተው አንድ ትልቅ ተራራ ከሆነ ታላላቅ ድንጋዮች ማምጣት አለበት።

የገጸ ምድሩ ሊቅ በድንገት ስሜቱ ተቀስቅሶ።

- ለካ አንተም የመጣኸው ከሩቅ ነው! አገር አሳሽ ነህ! እስኪ ያንተ ሕዋ አካል ምን እንደሚመስል ንገረኝ!

የገጸ ምድሩም ሊቅ መዝገቡን ዘረጋ እርሳሱንም ቀረጸ። የአግር አሳሾች ገለጻ በፊት በእርሳስ ነው የሚጻፈው። በቀለም የሚጻፈው ማስታወሻ አሳሹ መረጃዎቹን እስኪያቀርብ ድረስ ይቆያል።

- እህ? ሲል የገጸ ምድሩ ሊቅ ጠየቀ።

- አይ! የኔው እንኳ ብዙም ትኩረት አይስብም፣ በጣም አነስተኛ ነው። ሦስት እሳተ ገሞራዎች አሉኝ። ሁለቱ አልጠፉም፣ አንዱ ከስሟል። ግን ማን ያውቃል።

- ማን ያውቃል አለ የገጸ ምድሩ ሊቅ።

- አንዲት አበባም አለችኝ።

- አበባ አንመዘግብም አለ የገጸ ምድሩ ሊቅ::
- ምነዋ! በውበት ከሁሉም የምትበልጠው እሷ ነች::
- አበባዎች አላፊ ጠፊ ስለሆኑ፣ «አበባ አለው ገለባ» ይባላል::
- «አላፊ ጠፊ» ማለት ትርጒሙ ምንድነው?
- የገጸ ምድር ሥነ ጽሑፎች፣ አለ ሊቁ ከመጻሕፍት ሁሉ የበለጡ ብርቅዬ መጻሕፍት ናቸው:: ዘመን መቼም አይሽራቸውም:: ተራራ ቦታ ለወጠ ሲባል ተሰምቶም አይታወቅ:: ውቅያኖስ ውኃው ደርቆ ባዶውን ቀረ ሲባል ተሰምቶም አይታወቅ:: እኛ የምንጽፈው የማያልፈውን ነገር ነው::
- ታዳጊው ልዑል የሊቁን ንግግር አቋርጦ የከሰሙ እሳተ ገሞራዎች መልሰው ሊነቁ ይችላሉ አለ:: «አላፊ ጠፊ» ማለት ትርጒሙ ምንድነው?
- እሳተ ገሞራዎች ይጥፉም ይቀስቀሱ ለኛ ለውጥ የለውም አለ የገጸ ምድሩ ሊቅ:: ለኛ ዋናው ነገር ተራራው ነው:: የማይለወጥ ስለሆነ...::
- ዕድሜ ልኩን አንድ ጊዜ ጥያቄ ካቀረበ መልሱን ሳያገኝ የማይለቀው ታዳጊ ልዑል «አላፊ ጠፊ» ማለት ምን ማለት ነው? ብሎ በድጋሚ ጠየቀ::
- «በቅርቡ የመጥፋት አደጋ የሚያሠጋው» ማለት ነው::
- የኔ አበባ በቅርቡ የመጥፋት አደጋ ያስፈራዋል?
- እንዴ!

የኔ አበባ ጠፊ ረጋፊ ሆና መከላከያዋ አራት እሾኾች ብቻ ናቸው:: በዚህ ላይ ብቻዋን ትቻት ነው ካገሬ የወጣሁት::

መጀመሪያ ተጸጸተ፣ በኋላ ግን ራሱን አጽናንቶ፣

- ምን እንድጐበኝ ይመክሩኛል? ብሎ ጠየቀ::

- ምድር የተሰኘችውን ሕዋ አካል ብሎ መለሰለት፣ የገጸ ምድሩ ሊቅ። ዝናዋ ትልቅ ነው...።

ታዳጊው ልዑል አበባይቱን እያሰበ ወደዚያው ተጓዘ።



፲፭

ስለዚህ ሰባተኛው ሕዋ አካል ምድር ናት።

ምድር ተራ ሕዋ አካል አይደለችም! አንድ መቶ አሥራ አንድ ነገሥታት ይገኙባታል (ያውም ጥቂቁሮቹ ነገሥታት ሳይቈጠሩ)፣ ሰባት ሺህ የገጸ ምድር ሊቃውንት፣ ዘጠኝ መቶ ሺህ ነጋዴዎች፣ ሰባት ሚሊዮን ተኩል ሰካራሞች፣ ሦስት መቶ አሥራ አንድ ሚሊዮን ጉረኞች፣ ማለትም በጠቅላላው ሁለት ቢሊዮን ትልልቅ ሰዎች አሉ ማለት ነው።

መጠኗ ምን እንደሚያህል ለመግለጽ ያህል ኤሌክትሪክ ከመምጣቱ በፊት በስድስቱ አኅጉራት አራት መቶ ስድሳ ሁለት ሺህ አምስት መቶ አሥራ አንድ የመንገድ መብራት አብሪዎች ሠራዊት መቀለብ ያስፈልግ ነበር። ራቅ ብለው ሲያዩት ተግ ብሎ አንጸባራቂ ነበር። የሠራዊቱ እንቅስቃሴ እንደ ኦፔራ ውዝዋዜ ሥርዓት የያዘ ነበር። መጀመሪያ የኒው ዚላንድና የአውስትራሊያ አብሪዎች ይመጣሉ። መብራቶቻቸውን ያበሩና ሄደው ይተኛሉ። ቀጥለውም የቻይናና የሳይቤሪያ አብዎች ተራቸውን ውዘዋዜውን ይያያዛሉ። ከዚያ ወደ ጓዳ ገብተው ይሠወራሉ። ያን ጊዜ የራሻና የሕንድ መብራት አብሪዎች ተራ ይደርሳል። የአፍሪቃና የአውሮጳ ይቀጥላል። ከዚያ የደቡብ አሜሪካ፣ ብሎም የሰሜን አሜሪካ። ወደ መድረክ ሲወጡ ተራቸውን በፍጹም አያሳስቱም፤ ትርዒቱ አስገራሚ ነበር። ሰሜናዊ ዋልታ ላይ ብቻውን የቆመውን መብራት የሚያበራውና ደቡባዊ ዋልታ ላይ ብቻውን የቆመውን መብራት የሚያበራ የሥራ ባልደረባው እነዚህ ሁለቱ ብቻ የቦዘኔና የግድየለሽ ኑሮ ይኖሩ ነበር። ሥራ የሚሠሩት በዓመት ሁለት ጊዜ ነው።

፲፯

ንግግር እናሳምር ሲሉ በመጠኑ መዋሸት ይመጣል። ስለ መብራት አብሪዎቹ ስተርክላችሁ በጣም ሐቀኛ አልነበርኩም። መሬታችንን የማያውቁትን ሰዎች የተሳሳት ግንዛቤ በማግኘት አደጋ ላይ ልጥላቸው እችላለሁ። ምድር ላይ ሰዎች የያዙት ቦታ እጅግ አነስተኛ ነው። ምድር ላይ የሚኖሩት ሁለት ቢሊዮን ሰዎች ሕዝባዊ ስበሰባ ላይ እንደሚደረገው ትንሽ ተቀራርበው ቢቆሙ ሃያ ማይል በሃያ ማይል ስፋት ያለው አደባባይ ይበቃቸዋል። የሰውን ልጅ ዘር በአነስተኛ የፓሲፊክ ደሴት ውስጥ አጨናንቆ ማስፈር ይቻላል።

ትልልቆቹ ሰዎች እርግጥ አያምኑህም። ብዙ ቦታ የሚይዙ እንደ ወርካ የተንሰራፉ ይመስላቸዋል። ስለዚህ ሂሳቡን እንዲያወጡ ምከራቸው። አኃዞች በጣም ስለሚወዱ ስሌቱን አይጠሉትም። እርስዎ ግን በዚህ አታካች ሥራ ጊዜዎን አያጥፉ። ፋይዳ የለውም። እኔን ያምኑኛል።

ታዳጊው ልዑል መሬት ሲነካ ማንንም ባለማግኘቱ ተደነቀ። ተሳስቶ ሌላ ሕዋ ላይ ያረፈ መስሎት ፍራት ፍራት ማለት ሲጀምረው ጨረቃ የሚመስል ቀለበት አሸዋ ላይ ተላወሰ።

- ታዳጊው ልዑል እንዲያው በመላ «እንዴት አመሹ» አለ።

- እባቡም «እንደምን አመሸ» ብሎ መለሰ።

- ማን እሚባለው ሕዋ ላይ ነው እግር የጣለኝ? ብሎ ጠየቀ ታዳጊው ልዑል።

- «ምድር ላይ አፍሪካ ውስጥ» ብሎ መለሰለት እባቡ።

- እንዴ! ... ታዲያ እመሬት ላይ ሰውም የለ?

- ይኸ በረሃ ነው። በረሃ ውስጥ ማንም የለ። መሬት ሰፊ ናት፣ አለ እባቡ።

ታዳጊው ልዑል ድንጋይ ላይ ተቀመጠና ዓይኑን ወደ ሰማይ አንሥቶ፣

- ከዋክብት የሚያበሩት እያንዳንዱ ሰው አንድ ቀን ኮከቡን ፈልጎ ለማግኘት እንዲችል ይሆናል። የኔን ሕዋ አካል እያት። ልክ አናታችን ላይ ናት ... አቤት ርቀቷ!

- ታምራለች አለ እባቡ። እዚህ ምን ልታረግ መጣህ?

- ከአንዲት አበባ ጋር ችግር ገጥሞኛል አለ ታዳጊው ልዑል።

- ነው! አለ እባቡ።

እናም ሁለቱም ዝም አሉ።

- ታዳጊው ልዑል መልሶ፣ «ታዲያ ሰዎቹ የሉም?» አለ። በረሃ ውስጥ በመጠኑም ቢሆን ብቸኝነት አለ...።

- ብቸኝነቱስ በሰዎችም መካከል አይጠፋም አለ እባቡ።

ታዳጊው ልዑል ሲመለከተው ቆየና፣

«አስገራሚ አውሬ ነህ፤ ቅጥነትህ ጣት የሚያህል»... አለው።

- ኃያልነቴ ግን ከንጉሥ ጣት ይበልጣል አለ እባቡ።

ታዳጊው ልዑል ፈገግ አለ፣

- በጣም ኃያል አይደለህም ... እግር እንኳን የለህ! ... ከቦታ ቦታ መጓጓዝ አትችል ...

- ከመርከብ የበለጠ ሩቅ ልወስድህ እችላለሁ አለ፣ እባቡ።

በታዳጊው ልዑል ቁርጭምጭሚት ላይ እንደ ወርቅ አምባር ተጠመለለ፣

- ቀጥሎም «የምነካውን ሰው ወደመጣበት ወደ አፈርነቱ እመልሰዋለሁ» አለ። አንተ ግን ንጹሕ ነህ፤ የመጣኸውም ከኮከብ ነው...።

ታዳጊው ልዑል ምንም አልመለሰ።

- እንዳንተ ያለ ደካማ በዚህች በጥቁር ድንጋይ መሬት ላይ መገኘቱ ያሳዝነኛል። የሕዋ አካልህ በጣም ከናፈቀህ አንድ ቀን ልረዳህ እችላለሁ።



በመጨረሻ ታዳጊው ልዑል «አስገራሚ አውሬ ነህ፣ ቅጥነትህ ጣት የሚያህል... አለው::

- በጣም ገብቶኛልኮ፣ ግን ለምንድነው ንግግርህ ሁልጊዜ ምስጢር አዘል እንቆቅልሽ የሚሆንብኝ?

- እንቆቅልሹን ሁሉ እፈታዋለሁ፣ አለ እባቡ::

ሁለቱም ዝም አሉ::

፲፰

ታዳጊው ልዑል በረሃውን ሲያቋርጥ ከአንዲት አበባ በስተቀር ማንም አልገጠመው:: ሦስት ቅንጣት ብቻ ያላት አበባ፣ አልባሌ አበባ ...

- ጤና ይስጥልኝ አለ ታዳጊው ልዑል::

- ጤና ይስጥልኝ አለች አበባይቱ::

- ሰዎቹ የት ነው ያሉት? ብሎ ታዳጊው ልዑል በጨዋ ደንብ ጠየቀ::

- አበባዋ አንድ ቀን ሲራራ ነጋዴዎች ሲያልፉ አይቼ ነበር፣

- ሰዎች? ስድስት ሰባት የሚሆኑ ያሉ ይመስለኛል:: ካየኋቸው ዓመት አልፈዋል:: የት እንደሚገኙ ግን ፈጽሞ አይታወቅም:: ንፋስ ይዟቸው ይዞራል:: እነሱም ሥራቢሶች በመሆናቸው ብዙ ቅሬታ ይሰማቸዋል::

- ደህና ሰንብቺ አለ ታዳጊው ልዑል::

- ደህና ሁን አለችው አበባይቱ::

፲፬

ታዳጊው ልዑል አንድ ታላቅ ተራራ ላይ ወጣ። ከዚህ ቀደም የሚያውቀው እነዚያን ጉልበቱ የሚደርሱ ሦስት እሳተ ገሞራዎች ብቻ ነው። የጠፋውን እሳተ ገሞራ እንደ በርጩማ ይቀመጥበት ነበር። «ይኸን ከሚያህል ተራራ ላይ ከወጣሁ ሕዋ አካሉ በሙሉ ከነሰዎቹ ወለል ብሎ ይታየኛል» ... ብሎ አሰበ። ነገር ግን ጫፉቸው ሹል ከሆነ ሾጣጣ አለቶች በስተቀር ሌላ ምንም አልታየውም።

- እንዲያው በመላ እንዴት ዋላችሁ ሲል።

- የገደል ማሚቶው እንዴት ዋላችሁ ... እንዴት ዋላችሁ ... እንዴት ዋላችሁ ... ብሎ መለሰ፣ የገደል ማሚቶው።

- ማ ልበል? አለ፣



ታዳጊው ልዑል::

- ማ ልበል?... ማ ልበል?... ማ ልበል? ብሎ መሰሰ የገደል ማሚቶው::

«ምን ዓይነት ሕዋ አካል ነው! ብሎ አሰበ:: ከመድረቁ መሾሉ፣ በዚያ ላይ አሸበ መምስሉ:: ሰዎቹም ምናብ ያንሳቸዋል:: የተባለውን ነው የሚያስተጋቡት:: እኔ አገር አንዲት አበባ ነበረችኝ፣ ሁልጊዜ በንግግር ማንም የማይቀድማት ...»

፰

ታዳጊው ልዑል በአሸዋው በአረሁ በበረዶው መካከል ለረዥም ጊዜ ከተጓዘ በኋላ በመጨረሻ አንድ መንገድ ገጠመው:: መንገድ ሁሉ ሄዶ ሄዶ ሰዎቹ ወዳሉበት ነው የሚደርሰው::

- እንዴት ዋላችሁ አለ::

ጽጌሬዳዎች ያበቡበት አትክልት ነበር::

- እንዴት ዋሉ፣ አሉ አበቦቹ::

ታዳጊው ልዑል ትክ ብሎ አያቸው:: ሁሉም መልካቸው የሱኑ አበባ ይመስላል::


- እጅግ ደነቀውና «ማናቸሁ?» አላቸው::


«እኛ ጽጌሬዳዎች ነን» አሉት::

- «ይገርማል» አለ ታዳጊው ልዑል:: ...

ከዚያም ጥልቅ ሐዘን ተሰማው:: ያቺ የሱ አበባ «እኔ በፍጥረተ ዓለም ከሚገኙት አበባዎች ሁሉ በመልክ የሚመስለኝ የለም» ብላ ያወራችለት ትዝ ብሎት ነው:: አሁን አንድ መስክ ውስጥ ብቻ እነሆ አምስቱም ሺህ አበቦች መልካቸው አንድ ነው!

«ይኸንን ብታይ በጣም ይከፋት ነበር ... በኃይል ሳልይዟት ሐፍረቷን ለመሸፈን በሳል ለመሞት የደረሰች ትመስል ነበር::





እኔም የማስታምማት መምሰል ይኖርብኝ ነበር፣ አለበለዚያማ እኔንም ለማሳፈር ስትል የምሯን ሞታ ታርፈዋለች።

ሐሳቡን በመቀጠል «ብርቅ አበባ አለችኝ ብዬ በሀብቴ ስመካ ተራ ጽጌረዳ ሆና ተገኘች። አበባዬና ቁመታቸው ከኮልበቴ የማይደርስ ሦስት እሳተ ገሞራዎች ያውም አንደኛው ምናልባት ለዘለቄታው የከሰመ እነዚህን ይገዬ ትልቅ ልዑል እሆናለሁ ማለት አያዋጣኝም...» አለና እመስኩ ላይ ተኝቶ አለቀሰ።

፳፩

ቀበሮው ብቅ ያለው በዚህ ጊዜ ነው።

- ጤና ይስጥልኝ አለ ቀበሮ።

- ታዳጊው ልዑል በጨዋ ደንብ «አሜን፣ ጤና ይስጥልኝ» አለና ዘወር ቢል ምንም የለ።

- እዚህ እቱሩ ዛፍ ሥር ነኝ ሲል ድምፁን አሰማ...::

- ማነህ? አለ ታዳጊው ልዑል::

መልክህ ማማሩ...::

- ቀበሮው ሲመልስ «ቀበሮ ነኝ» አለ::

- ና አብረን እንጫወት ብሎ ጋበዘው ታዳጊው ልዑል:: እኔ በጣም አዝኛለሁ::...

-ካንተ ጋር መጫወት አልችልም አለው ቀበሮው:: እኔ የአውሬነት ባሕርይ እንዲለቀኝ አልምዶ ገራም አላደረጉኝም::

ታዳጊው ልዑል አሰበበትና፣


- «አልምደው» ማለት ምን ማለት ነው? አለው::

- አንተ የዚህ አገር ሰው አይደለህም፣ አለው ቀበሮ፣ ምን እየፈለግህ ነው?

- እኔ እምፈልገው ሰዎችን ነው:: አለ ታዳጊው ልዑል:: «አልምደው» ማለት ምን ማለት ነው?

- ሰዎች ጠመንጃ አላቸው፣ አደንም ይወጣሉ:: ችግር ነው! ዶሮም ያረባሉ:: ሌላ ሙያ የላቸውም:: ዶሮ ነው የምትፈልገው?

- የለም አለ ታዳጊው ልዑል:: እኔ የምፈልገው ወዳጅ የሚሆነኝ



ነው:: «አልምደው» ማለት ምን ማለት ነው?

- በጣም የተረሳ ነገር ነው አለ ቀበሮው:: «ትስስር መፍጠር» ማለት ነው...::

- ትስስር መፍጠር?

- ነውና አለ ቀበሮው:: ሳይህ ገና ታዳጊ ነህ:: በመቶ ሺህ ከሚቈጠሩ ታዳጊ ልጆች በምንም አትለይም:: ለኔም አታስፈልገኝም:: እኔም አላስፈልግህ:: እኔ ላንተ ከመቶ ሺህ ቀበሮዎች ያልተለየሁ ቀበሮ ነኝ:: ካለመድከኝ ግን እኔና አንተ እንፈላለጋለን:: አንተ ለኔ በዚህ ዓለም ውስጥ የብቻዬ ትሆናለህ:: እኔም ላንተ በዚህ ዓለም የብቻህ እሆናለሁ::...

- እየገባኝ ነው አለ ታዳጊው ልዑል:: አንድ አበባ አለች... ያለመደችን ይመስለኛል...

- ሊሆን ይችላል አለ ቀበሮው:: ዓለም ላይ ብዙ ዓይነት ነገር ይታያል...

- አይ ዓለም ላይ አይደለም አለ ታዳጊው ልዑል::

ቀበሮው ግራ ገባው፣

- ሌላ ሕዋ አካል ላይ ነው አልከኝ?

- አዎ::

- እዚያ ሕዋ አካል ላይ አዳኞች አሉ?

- የሉም::

- ወይ ታሪክ! ዶሮዎችስ?

- የሉም::

- መቸም አሟልቶ አይሰጥ አለ ቀበሮ በትካዜ::

ቀበሮ ወደ ቀድሞ ሐሳቡ ተመለሰና፣

- የኔ አኗኗር ያሰለቻል:: እኔ ዶሮ አድናለው፣ ሰዎች እኔን ያድናሉ:: ዶሮ ከዶሮ ይመሳሰላል፣ ሰውም ከሰው:: ስለዚህም ነው ስልችት የሚለኝ:: አንተ ለመድከኝ ግን ፀሐይ ወጣልኝ ማለት ነው:: የምሰማው የኩቴ ድምፅ ከሌሎቹ ሁሉ የተለየ ይሆናል ማለት ነው:: ሌሎቹ በአረማመዶች ጉድጓድ ያስገቡኛል::

ያንተ ግን እንደ ሙዚቃ ከጐሬ ያስወጣኛል። ከዚህ በስተቀር እሰቲ ተመልከት እዚያ ማዶ የስንዴ ማሳዎች ይታዩሃል? እኔ ዳቦ አልበላም። ስንዴ ለኔ ጥቅም የለውም። የስንዴ ማሳዎች ሳይ ምንም ትዝ የሚለኝ ነገር የለም። የሚያሳዝን ነገር ነው! ጸጉርህ ወርቅማ ነው። ለማዳ ካደረግኸኝ ሁሉ ነገር ግሩም ይሆናል። ስንዴው ሲደርስና ወርቅ ሲመስል አንተን ያስታውሰኛል። እስንዴውም ላይ የሚነፍሰውን ነፋስ ድምፁን መውደድ እጀምራለሁ። ...

ቀበሮው ዝም አለና ታዳጊውን ልዑል በረጅሙ አስተዋለና፣

- እባክህ ... ለማዳ አድርገኝ አለው!

- «ማልመድ ምን ገዶ» ብሎ መለሰለት ታዳጊው ልዑል፤ «ጊዜ ያጥረኛል እንጂ» ወዳጆች ፈልጌ ማበጀት አለብኝ። ሌላም ለማወቅ የምፈልገው ብዙ ነገር አለ።

- «ማወቅ የሚቻለው ያለመዱትን ነገር ብቻ ነው» አለ ቀበሮው። ሰዎች ምንም ነገር ለማወቅ ጊዜ የላቸውም። እነጋዴዎች ዘንድ የሚገዙት ሁሉ ሥራው ያለቀለት ነገር ነው። ወዳጅ የሚሸጥ ነጋዴ ስለሌለ ሰዎች ወዳጅ ይቸግሯቸዋል። ወዳጅ ካማረህ እኔን አልምደኝ!

- ምን ይሻላል? አለ ታዳጊው ልዑል።

- ትእግስተኛ መሆን ነው ብሎ ቀበሮው መለሰለት።

- መጀመሪያ እንዲያው ዝም ብለህ እሣሩ ላይ ከኔ ራቅ ብለህ ቁጭ ትላለህ። እኔ በጐን አይሃለሁ፣ አንተ ግን ምንም አትልም። ነገር ሲበዛ ጠብ ያበቅላል። በየቀኑ ግን ቀረብ እያልክ መቀመጥ ነው...

በማግሥቱ ታዳጊው ልዑል ተመልሶ መጣ።

- በዚያው ሰዓት ብትመጣ ይሻል ነበር አለው ቀበሮ። ለምሳሌ ከቀትር በኋላ በአሥር ሰዓት ብትመጣ እኔ ደስታ የሚሰማኝ ገና ከዘጠኝ ጀምሮ ይሆናል። ሰዓቱ በገፋ መጠን ደስታዬ እየላቀ ይሄዳል። አሥር ሰዓት ሲሞላ መወራጨትና መስጋት እጀምራለሁ፣

የደስታው ዋጋ ገባኝ ማለት ነው! በፈለግኸው ሰዓት ከመጣህ ግን ልቤን አለባብሼ የምቆይበት ሰዓት ይጠፋኛል። ለሁሉም ሥርዓት ያሻዋል።

- ሥርዓት ማለት ምን ማለት ነው? አለ ታዳጊው ልዑል።

- እየተረሱ ከሄዱት ነገሮች አንዱ ነው አለ ቀበሮው። አንዱን ቀን ከሌላው፣ አንዷን ሰዓት ከሌሎቹ የተለየች የሚያደርጋት ሥርዓት ነው። ለምሳሌ እኔን የሚያድኑቱ ግለሰቦች የራሳቸው ሥርዓት አላቸው። ሐሙስ ሐሙስ ከመንደሩ ኮረዳዎች ጋር ይደንሳሉ። ስለሆነም ሐሙስ የቀን ቅዱስ ነው! እስከ ወይኑ ተክል ድረስ እንሸራሸራለሁ። አዳኞቹ በፈለጉት ቀን ቢደንሱ ኖሮ ቀኖቹ ሁሉ እየተመሳሰሉ እረፍት አጣ ነበር።

እንዲሁ እያለ ታዳጊው ልዑል ቀበሮውን ለማዳ አደረገው። መሄጃው ሰዓት ሲደርስ፡

- አይ! አለ ቀበሮው ... ማልቀሴ ነው።

- በገዛ እጅህ አለው ታዳጊው ልዑል፣ እኔ ክፉ ነገር አልተመኘሁልህ፣ ለማዳ እንዳደርግህ የፈለግኸው ራስህ ነህ።...

- እርግጥ ነው አለ ቀበሮው።

- ስታለቅስ ልትኖር ነው! አለው ታዳጊው ልዑል።


- መጠርጠሩ! ብሎ መለሰለት ቀበሮው።

- ብታለቅስ ምን ታገኛለህ!

- የስንዴው ማሳ ጎብረ ቀለም እስካለ ምን ገዶ።

ቀጥሎም፣





ለምሳሌ ከቀትር በኋላ በአሥር ሰዓት
ስትመጣ እኔ ደስታው የሚሰማኝ ዋና
ከዘጠኝ ሰዓት ጀምሮ ነው።

- በል ሂድና ጽጌረዳዎቹን ጠይቃቸው። ያንተ አበባ በዓለም ላይ ብርቅዬ መሆኗን ትገነዘበዋለህ። ስትመለስ ትሰናበተኛለህ። ያን ጊዜ አንድ ምስጢር በስጦታ መልክ እነግርሃለሁ።

ታዳጊው ልዑል ጽጌረዳዎቹን ሊጠይቅ ሄደ።

- በፍጹም የኔን ጽጌረዳ አትመስሉም፣ ገና ለምንም አትበቁም አላቸው። ማንም ለማዳ አላደረጋችሁም፣ እናንተም ማንንም አላለመዳችሁ። የኔ ቀበሮ በነበረበት ሁኔታ ናችሁ። እሱ በመቶ ሺህ ከሚቈጠሩ ሌሎች ቀበሮዎች በምኑም አይለይም ነበር። ግን ወዳጄ አድርጌው አሁን በዓለም ላይ አንድና ብቸኛ ብርቅ ቀበሮ ሆኗል።

ጽጌረዳዎቹም በጣም ተሸማቀቁ።

- ንግግሩን በመቀጠል «ታምራላችሁ ግን ባዶ ናችሁ» አላቸው። ለናንተ ብሎ የሚሞት የለም። እርግጥ ለተራ መንገደኛ የኔይቱ አበባ እናንተን ትመስለው ይሆናል። እሷ ግን አንድ ብቻዋን ከናንተ ሁሉ ትበልጣለች፣ ምክንያቱም ውኃ ያጠጣኋት እሷን ስለሆነ ነው። ክዳን ያበጀሁላት እሷ ነች። ግርዶሽ ሠርቼ ያስጠለልኳትም እሷን ነው። አባ ጨጓሬዋን (ሁለት ሦስት ለቢራቢሮነት አስተርፌ) የገደልኩላት እሷ ነች። ቅሬታዋን ስታሰማኝ ወይም ስትጐርርብኝ የሰማኋት፣ አልፎ አልፎም ዝም ስትል ያየኋት እሷ ነች። የኔ ጽጌረዳ ስለ ሆነች።

ከዚያም ወደ ቀበሮው ተመለስ፣

- ደህና ሁኑ አለ ...

- ደህና ሁን አለው ቀበሮው። የማካፍልህ ምስጢር እነሆ፤

- በስሜት ካላዩት አይጠራም። ፍሬ ነገር ለዓይን እንግዳ ነው።

- ታዳጊው ልዑል እንዳይረሳው በድጋሚ፣ «ፍሬ ነገር ለዓይን እንግዳ ነው» አለ።

- ያንተ ጽጌረዳ ይህን ያህል ዋጋ ያገኘችው አንተ ባጠፋህላት ጊዜ ምክንያት ነው።



እመስኩ ላይ ተኝቶ
አለቀሰ።

- «እኔ ለጽጌረዳዬ ያጠፋሁላት ጊዜ ነው» አለ ታዳጊው ልዑል እንዳይረሳው::

- ሰዎች ይኸንን እውነት ረስተውታል አለ ቀበሮው:: አንተ ግን መርሳት የለብህም:: ላለመድከው ነገር የዘለዓለም ኃላፊነት አለብህ:: ለጽጌረዳህ ተጠያቂው አንተ ነህ...

- ለጽጌረዳዬ ተጠያቂው እኔ ነኝ አለ ታዳጊው ልዑል እንዳይረሳው::

ሻያ

- እንዴት ዋላችሁ! አለ ታዳጊው ልዑል::

- ይመስገነው! አለ የሐዲድ መሥመር ተቈጣጣሪው::

- እዚህ ምን ያደርጋሉ? አለው ታዳጊው ልዑል::

- መሥመር ተቈጣጣሪው፣ «መንገደኞቹን በአንዳንድ ሺህ እየደለደልኩ ነው:: የሚያጓጉዙአቸውን ባቡሮች አንዱን ወደ ቀኝ አንዱን ወደ ግራ እያሰማራሁ ነው::»

በዚህ ጊዜ አንድ ባለመብራት ፈጣን ባቡር እንደ ነጐድጓድ እያጒረመረመ ሲያልፍ የተቈጣጣሪውን ሰንተርያ አንቀጠቀጠው::

- ምን አጣደፋቸው አለ ታዳጊው ልዑል:: ምንድነው የሚፈልጉት?

- ባቡር ነጂው ራሱ ለምን እንደሚጣደፍ አያውቀውም አለ መሥመር ተቈጣጣሪው::

አሁንም ሌላ ባለመብራት ፈጣን ባቡር በተቃራኒው አቅጣጫ አጒረመረመ::

- የቅድሞቹ መመለሳቸው ነው? አለ ታዳጊው ልዑል::

- እነዚያ አይደሉም አለ ተቄጣጣሪው:: ቅያሪ ነው::

- የነበሩበትን ጠልተውት ነው?


- ሰው ባለበት ቦታ መች ተደስቶ ያውቃል አለ መሥመር ተቄጣጣሪው:: እነደገና ሦስተኛ ፈጣን ባለመብራት ባቡር ነጐድጓዱን አሰማ::

- የመጀመሪያዎቹን ተጓዦች እያሳደዱ ነው? አለ ታዳጊው ልዑል::

- ምንም የሚያሳድዱት ነገር የለም አለ መስመር ተቄጣጣሪው:: እዚያ ውስጥ እያንቀላፉ ወይም እያዛጋቸው ነው:: ልጆቹ ብቻ ናቸው አፍንጫቸውን እመስተዋቱ ላይ የሚደፈጥጡት::

- የሚፈልጉትን የሚያውቁ ልጆቹ ብቻ ናቸው አለ ታዳጊው ልዑል:: በጨርቅ ለተሠራች አሻንጉሊት ጊዜያቸውን ያባክናሉ፣ ለነሱ ትልቅ ነገር ነች፣ የወሰዱባቸው እንደ ሆነ ያለቅሳሉ...::

- ዕድለኞች አለ መሥመር ተቄጣጣሪው::



፰፫

- እንዴት ዋላችሁ? አለ ታዳጊው ልዑል።
- ይመስገነው አለ ነጋዴው።

ውኃ ጥም የሚያረኩ ጥራት ያላቸው እንክብሎች ነጋዴ ነው። ውኃ እንዳይጠማ በሳምንት አንዷን መዋጥ ብቻ ነው።

- ይህን ለምን ትሸጠዋለህ? አለ ታዳጊው ልዑል።
- ነጋዴው ሲመልስ፣ «በከፍተኛ ደረጃ ጊዜ ስለሚቆጥብ ነው» አለ። ባለሙያዎች ያካሄዱት ጥናት አለ። በሳምንት ሃምሳ ሦስት ደቂቃ የጊዜ ቁጠባ ለማድረግ ያስችላል።
- ሃምሳ ሦስቱን ደቂቃ ምን ምን ያደርጉበታል?
- እንደ ፈለጉ ይጠቀሙበታል...።
- ታዳጊው ልዑል በሆዱ፣ «እኔ የማጠፋው ሃምሳ ሦስት ደቂቃ ቢኖረኝ ቀስ እያልኩ ምንጭ ወዳለበት አዘግም ነበር» አለ።

፰፬

በረሃ ውስጥ አደጋ ከደረሰብኝ ሳምንት ሲሆነው፣ የነጋዴውን ታሪክ ያዳመጥኩት የውኃ ስንቄን መጨረሻ ጠብታ እየጠጣሁ ነበር።

- እሺ! አልሁት ታዳጊውን ልዑል። «ያወሳሃቸው ትዝታዎች በጣም ደስ ይላሉ። እኔ ግን ኤሮፕላኔን ገና አልጠገንኩም፣ የምጠጣውም የለኝ፣ እናም እኔም እንዳንተ ምንጭ ወዳለበት ቀስ እያልኩ ባዘግም ደስ ይለኝ ነበር!»
- ወዳጄ ቀበሮ... አለኝ ታዳጊው ልዑል።
- ወዳጄዋ ቁም ነገሩ ስለ ቀበሮው አይደለም!

- ለምን?

- በውኃ ጥም መሞታችን ስለሆነ...::

አስተሳሰቤ አልገባውም ነበርና፣ ሲመልስልኝ እንዲህ አለ፣

- መሞታችን ቢሆን አንድ ወዳጄን ማትረፉ አይከፋም::

እኔ የቀበሮ ወዳጅ በማግኘቴ ደስ ብሎኛል...::

በልቤ «ይኸ ልጅ ሊደርስበት የሚችለውን አደጋ አልተገነዘበውም ብዬ አሰብኩ:: እሱ አይርበው አይጠማው:: ትንሽ ፀሐይ ካገኘ ይበቃዋል...::

እሱ ግን አየት አደረገኝና ለሐሳቤ መልስ ሲሰጥ፣

- እኔም ውኃ ጠማኝ የውኃ ጉድጓድ እንፈልግ አለኝ...::

ስልችት አለኝና «ጭው ያለ በረሃ ውስጥ በዳበሳ የውኃ ጉድጓድ መፈለግ ምን ትርጉም አለው:: ያም ሆኖ ጉዞውን ተያያዝነው::

ለሰዓታት አንድ ቃል ሳይወጣን ከተጓዝን በኋላ መሸና ከዋክብቱ ማብራት ጀመሩ:: በውኃ ጥሙ ምክንያት ትንሽ ስላተኩለኝ ከዋክብቱ የሚታዩኝ እንደ ሕልም ነበር:: የታዳጊውም ልዑል ንግግር በምናቤ ውስጥ ይጉላላ ነበር::

- አንተም ውኃ ጠምቶሃል ብዬ ጠየቅሁት::

መልስ አልሰጠኝም:: እንዲያው በቀላሉ፣

- ውኃም ለልብ ጥሩ ሊሆን ይችላል አለኝ...::

መልሱ አልገባኝም ነበርና ዝም አልኩ...:: ጥያቄ ባበዛበት ጥሩ እንደማይሆን አውቅ ነበር::

ደክሞት ነበር:: ቁጭ አለ:: እኔም አጠገቡ ተቀመጥኩ:: ጸጥ ብሎ ትንሽ ቆየና፣

- ከዋክብቱ የሚያምሩት በአንዲት በማትታይ አበባ ምክንያት ነው... አለ፣ ንግግሩን በመቀጠል፣

- እንዴ! ብዬ መለስኩለትና በጨረቃ ወገግታ የአሸዋውን ሰንበር በጥሞና አስተውል ጀመር::

- በረሃ ውብ ነው አለ:: በንግግሩ ላይ በማከል:: ጥርጥር

የለውም:: እኔ ቀድሞውንም በረሃ እወድ ነበር:: አሸዋ ስንበር ላይ መቀመጥ ነው:: ምንም የሚታይ የለም:: ምንም አይሰማም:: ያም ሆኖ በጸጥታ የሚያንጸባርቅ ነበር አለ...::

- ለበረሃ መልክ የሚሰጠው ባልታወቀ ቦታ ምንጭ ተሸሽጎ መገኘቱ ነው ... አለ ታዳጊው ልዑል::

የአሸዋ ምስጢራዊ ነጸብራቅ መኖሩን በድንገት መገንዘቤ ደነቀኝ:: ልጅ ሆኜ የምኖርበት ቤት የቆየ ስለ ነበረ ቅርስ ተቀብሮበታል የሚል አፈ ታሪክ ይነገራል:: እርግጥ ቅርሱን ያገኘ የለም፣ የፈለገም ሰው መኖሩ ያጠራጥራል:: ለቤቱ ግን አድናቆት አበርክቶለታል:: ቤቴ በማጎፀኗ ምስጢር ይዛለች...::

- አዎ! አልኩት ታዳጊውን ልዑል:: «ቤትም ይሁን ከዋክብት ወይም በረሃ ውበት የሚሰጣቸው ምን እንደሆነ በዓይን ማየት አይቻልም!

- ከቀበሮዬ ጋር መስማማትህ ደስ ብሎኛል::

ታዳጊው ልዑል እንቅልፉ መጥቶ ስለ ነበረ ታቀፍኩትና ጉዞዬን ቀጠለኩ:: ስሜት አደረብኝ:: ተሰባሪ ሀብት የተሸከምኩ ይመስለኛል:: እምድር ላይ ከዚህ የበለጠ ተሰባሪ ነገር ያለ አይመስለኝም:: በጨረቃ ብርሃን ነጭ ግንባሩን፣ የተከደኑ ዓይኖቹን፣ በነፋስ የሚውለበለበውን የጸጉሩን ቁንጮ እያየሁ «ይኸ የማየው ሁሉ ቅርፊት ነው:: ዋናው ለዓይን አይታይም» እል ነበር...

ከንፈሮቹ ተገልጠው በከፊል ፈገግ ሲል «እንቅልፍ ለያዘው ልዑል ይህን ያህል ስሜት ያደረብኝ ለአንዲት አበባ የሚያሳየው ታማኝነት፣ በተኛበትም ቢሆን እንደ መቅረዝ ብርሃን በልቡ የሚያበራው የጽጌረዳይቱ ሥዕል ነው::» ... ብዬም በልቤ አሰብኩ:: ከዚህም የበለጠ ተሰባሪ እንደሚሆን ግምት ነበረኝ:: መብራትን ተጠንቀቆ መንከባከብ ያሻል፣ ነፋስ ሽው ቢል ያጠፋዋልና...::

ሳዘግም አድሬ ጐሕ ሲቀድ የውኃ ጉድጓዱን አገኘሁት...::



ሣሁ፣ ገመዱን ነሳው፣
መጠመሩን ሞከረው።።

፳፭

- ሰዎች፣ አለ ታዳጊው ልዑል፣ በየጅረቱ እየዘለሉ ይገባሉ ግን የሚፈልጉትን ማወቅ ይሳናቸዋል። በዚህ ጊዜ ይቅበጠበጣሉ ይሽከረከራሉ...

ቀጥሎም፣

- ዋጋ የለውም ... አለ።

ያገኘነው ጉድጓድ የሰሐራን ጉድጓዶች አይመስልም። የሰሐራ ጉድጓድ በቀላሉ የተቈፈረ አሸዋ ነው። ይኸኛው ግን የመንደር ጉድጓድ ይመስላል። ነገር ግን ባካባቢው መንደር ስላልነበረ በሕልሜ ነው በእውኔ ብዬ ጠረጠርኩ።

- «ይገርማል» አልኩት ታዳጊውን ልዑል ዝግጅቱ የተሟላ ነው፣ መዘውሩም ባልዲውም ገመዱም አለ...።

ሣቀና ገመዱን ነካው፣ መዘውሩን ሞከረው። ነፋስ ለረኸም ጊዜ ሳይነሣ ቀርቶ እንዳልተንቀሳቀሰች የጣራ ሽክርክሪት መዘውሩ ሲጢጥ ሲጢጥ አለ።

- ይሰማሃል አለ ታዳጊው ልዑል ጉድጓዱን ከተኛበት ስንቀሰቅሰው ጊዜ መዝፈን ጀመረ ...

እንዲቸገር አልፈለግሁም ነበርና፡

- እሰቲ ለኔ ተውልኝ ላንተ በጣም ይከብድሃል አልኩት። ቀስ እያልኩ ባልዲውን ጒድጓዱ ገደፍ ድረስ ስቤ አወጣሁና እገደፉ ላይ አመቻችቼ አስቀመጥኩት። የመዘውሩ ዝማሬ ሳያቋርጥ የሚሰማኝ ይመስለኛል። በሚንቀጠቀጠው ውኃ ውስጥ ፀሐዩ ሲንቀጠቀጥ ይታየኛል።

-«ያ ውኃ ጠጡኝ ጠጡኝ ይላል»... አለ ታዳጊው ልዑል።

እኔም ምን እንደ ፈለገ ገባኝ!

ባልዲውን እስከ ከንፈሩ ድረስ ከፍ አደረግሁለት። ዓይኑን

ጨፍኖ ጠጣ። እንደ እርጎ አንጀቱን አራሰው። ያ ውኃ ከምግብ የተለየ ነበር። ከጨረቃ በታች ጉዞ፣ ልብ የሚያረካ በሕፃንነቴ ለልደት በዓል የሚመጣልኝን ስጦታ ነጻብራቅ የሚያጐናጽፉት የገና ዛፉ መብራት የመንፈቀ ሌሊቱ ማጎሌት የፈገግታዎቹ ልስላሴ ነበር።

- ታዳጊው ልዑል ሲመልስለት «ያንተ አገር ስዎች አምስት ሺህ አበባዎች በአንድ ጓሮ ይተክላሉ...። ያም ሆኖ ግን የሚፈልጉትን አያገኙበትም።

- እርግጥ የሚፈልጉት አያገኙትም ብዬ መለስኩለት ...

- ታዲያ እኮ የሚፈልጉት ነገር ባንዲት ጽጌረዳ ወይም ባንድ ጥርኝ ውኃ ሊገኝ ይችላል...

- እውነት ነው አልኩት።

ታዳጊው ልዑልም ሲመልስልኝ፣

- ዓይን ያያል እንጂ አያስተውልም። መሻት በልብ ነው።

- ውኃዬን ጠጥቼ ትንፋሼ ተመልሷል። ሲነጋጋ የአሸዋው ቀለም ማር ይመስላል። ይህ ማር የመሰለ ቀለም እኔንም ያስደስተኛል። ሐዘን ለምኔ?...።

- እንደገና አጠገቤ ተቀምጦ የነበረው ታዳጊው ልዑል ቀስ ብሎ፣ «የገባኸውን ቃል መጠበቅ አለብህ» አለኝ።

- ምን የገባሁት ቃል አለ?

- መች አጣኸው ... ለበጌ መሸለቢያ ... ለዚያች ለአበባ ኃላፊነት አለብኝ!

የሥዕል ንድፎቼን ከኪሴ አወጣሁ። ታዳጊው ልዑል አይቶ ሣቀና፣

- ዋርካዎችህ ወደ ጐመንነት ይወለዳቸዋል...።

- ኧረ!

እኔ ያንን ያህል ስኰራባቸው!

- ቀበሮህ... ጆሮዎቹ ትንሽ ወደ ቀንድነት ይወለዳቸዋል... በዚህ ላይ በጣም ረዝመዋል!

አሁንም ሣቀ፤

- ጨከንክብኝ አንተዬ ከድፍን ዘንዶና ከክፍት ዘንዶ በስተቀር ሌላ ነገር መሣል አላውቅም ነበር::

- አይ አትጨነቅ ልጆች አያመልጣቸውም::

በዚህ ጊዜ መሸለቢያውን ሥዬ ስሰጠው አንጀቴ ቡጭ ቡጭ አለ::

- እኔ እማላውቀው ነገር አቅደሃል...::

እሱ ግን አልመለሰልኝም::

- ታውቃለህ መሬት እምትባለው ሕዋ አካል ላይ ከወደቅሁ ነገ አንድ ዓመቴ መሆኑ ነው ... አለኝ::

ደግሞ በዝምታ ትንሽ ቆየና፣

- እዚህ አካባቢ ነው የወደቅሁት አለኝ::

ከዚያም ፊቱ በርበሬ መሰለ::

ለምን እንደሆነ አላውቅም እንደ ገና ግራ የሚያጋባ ሐዘን ተሰማኝ:: ሆኖም አንድ ጥያቄ በሐሳቤ መጣብኝ::

- እንግዲያውማ ያለፈው ሳምንት ሚት ስንተዋወቅ ሰው ካለበት አካባቢ 1852 ኪሎሜትር ርቀት ላይ ዝም ብለህ ብቻህን ትንሽራሽር የነበረው ያለ ምክንያት አልነበረም ማለት ነዋ? ወደ ወደቅህበት መመለስህ ነበር? አልኩት::

ታዳጊው ልዑል እንደ ገና ፊቱ ቀይ ሆነ::

እኔም ስፈራ ስቸር፣

- ዓመት የሞላህበትን ቀን ለማክበር ይሆን?... አልኩት::

ታዳጊው ልዑል አሁንም ቀይ ሆነ:: ሲጠይቁት አይመልስም ነበር፣ ግን ቀይ መሆን ያው «አዎ» ማለት አይደለም እንዴ?

- ወይኔ አልኩት፣ ፍራት ፍራት አለኝ...::

እሱ ግን፣

- አሁን መሥራት አለብህ:: ወደ መኪናህ ተመልሰህ መጓዝ አለብህ:: እዚህ እጠብቅሃለሁ:: ነገ ማታ ተመልሰህ ና...

እኔ ግን መንፈሴ አልተረጋጋም ነበር:: የቀበሮው ነገር ትዝ ይለኛል:: መለማመድ ከመጣ ትንሽ ማልቀስ አይቀርም::...

፳፯

ከውኃ ጉድጓዱ አጠገብ የአሮጌ ካብ ፍርስራሽ ነበር። በማግሥቱ ማታ ከሥራዬ ስመለስ ታዳጊው ልዑል ሆዬ አፋፉ ላይ እግሮቹን አንጠልጥሎ እንደ ተቀመጠ ከሩቅ አየሁት። ሲነጋገርም ይሰማኛል፣

- «አታስታውስም? እንዴ ልክ እዚህ አልነበረም!» ይላል።

- አዎ፣ እዎ፣ ቀኑ ትክክል ነው፣ ቦታው ግን እዚህ አይደለም...።

ወደ ግንቡ ማምራቴን ቀጠልኩ። ማንም አይታየኝ፣ ሌላም ድምፅ አይሰማኝ። ታዳጊው ልዑል ግን አሁንም መልስ ሲሰጥ፣... እህሳ። አሸዋው ላይ የእግሬ ፈለግ የት እንደ ጀመረ ይታይሃል። እዚያ ላይ እኔን መጠበቅ ብቻ ነው። ዛሬ ሌሊት እደርሳለሁ።

እግንቡ አጠገብ ለመድረስ ሃያ ሜትር ነው የቀረኝ ግን አሁንም ቢሆን ማንም አይታየኝ።

ታዳጊው ልዑል አንድ አፍታ ዝም አለና ንግግሩን በመቀጠል፣

- መርዝህ ፍቱን ነው? ሥቃዩ እንደማይቆይብኝ እርግጠኛ ነህ አለው?

ቀጥ ብዬ ቆምኩ፣ ልቤ ትርትር አለ፣ አሁንም አልገባኝም።

- አሁን በል ወጊድልኝ ... ልውረድበት! አለው።

በዚህ ጊዜ እኔም ራሴ ወደ ግንቡ ሥር ዓይኔን ጣል ሳደርግ ወደ ኋላ ተፈናጠርኩ። መርዙ በሠላሳ ሰከንድ ሰው የሚገድለው ዓይነት ቢጫ እባብ ታዳጊው ልዑል ላይ አንገቱን አስግጎችኋል። ሽጉጤን ለማውጣት ኪሴን እየፈተሽኩ ወደ ፊት ሩጫዬን ስጀምር እባቡ እርምጃዬን ሰምቶ ኖሮ አሸዋው ላይ ሸለል አለና ፍልቅታውን እንዳቋረጠ ፏፏቴ ሰብሰብ ብሎ በአለቶቹ መካከል እየተቅጨለጨለ በእርጋታ ሹልክ ብሎ ሄደ።

ልክ እግንቡ ሥር ሲደርስ የኔ ታዳጊ ልዑል ፊቱ እንደ በረዶ ነጭ ሆኖ እክንዴ ላይ ውድቅ አለ።

- የምን ታሪክ አመጣህብኝ! ብለህ ብለህ ከአባቦች ጋር ማውራት ጀመርክ?

አውልቆት የማያውቀውን ወርቅማ ያንገት ልብስ ፈታሁለት:: ጆሮግንዱን አራስኩለትና ውኃ አጠጣሁት:: ከዚያ ምንም ልጠይቀው አልደፈርኩም:: ትኩር ብሎ አየኝና አንገቴ ላይ ጥምጥም አለ:: ልቡ ሲመታ በጥይት ቄስሎ እንደሚሞት የወፍ ልብ ትርታ ነበር:: እንደዚህ አለኝ፣

- ለመኪናህ የሚያስፈልገውን ዕቃ ስላገኘህ ደስ ብሎኛል:: እንግዲህ ወዳገርህ መሄድ ልትችል ነው...::

- እንዴት አወቅህ!

እኔ የመጣሁት ሥራዬ ከምጠብቀው በላይ የተሳካልኝ መሆኑን ልነግረው ነበር!

ላቀረብኩለት ጥያቄ ምንም መልስ አልሰጠኝ፣ ግን በንግግሩ ላይ በማከል፣

- እኔም ዛሬ አገሬ እገባለሁ ... አለኝ::

ከዚያም በትካዜ፣

ኻንተ አገር በጣም ይርቃል...:: መንገዱም የበለጠ ያስቸግራል::

አንድ በጣም ልዩ የሆነ ነገር በአእምሮው ውስጥ እንደሚጉላላ ተሰማኝ:: እንደ ሕፃን ልጅ እቅፍ ሳደርገው ይገፍ ላስቀረው በማልችልበት ሁኔታ ዥው ብሎ አዘቅት እንደሚወርድ ሰው ሲንሸራተት ይሰማኛል...::

ኩስተር ብሎ ዓይኑን አሻግሮ ወርወር አደረገና፣

- በግህ አለኝ:: የበጉም ሣጥን አለኝ፣ መሸለቢያውም አለኝ:: ...


ፊቱ ፈገግ ቢልም ትካዜ ይታይበታል::

ብዙ ቆየሁ፤ ቀስ እያለ ሰውነቱ ሲሞቅ ይሰማኛል::

- ማሙዬ፣ ፍራት ይዞህ ነው...::

ፍራትማ ይዞታል! ግን ቀስ ብሎ እየሣቀ፣

- ዛሬ ማታ የበለጠ የሚያስፈራኝ ... አለ::



«አሁን በል ወጊድልኝ ...
ልውረድበት!» አለው።

ልመልሰው የማልችለው አደጋ እንደገና በሐሳቤ ግጥም አለብኝና ሰውነቴ በስሜት ቀዘዘ። ያንን ሣቁን ዳግመኛ መስማት አለመቻሌን ማሰቡ ብቻ የማልችለው ስሜት እንደሚያሳድርብኝ ገባኝ። ሣቁ ለኔ የምድረበዳ ምንጭ ነው።...

እሱ ግን፣

- ዛሬ ሌሊት ዓመት መሆኑ ነው። የኔ ኮከብ ልክ አምና እወደቅሁበት ቦታ አናቱ ላይ ትደርሳለች...

- ማሙዬ፣ ይኸ ሁሉ የአባብ የቀበሮና የኮከብ ታሪክ ቅዠት አይደለም? ...

- ለጥያቄዬ መልሰ አልሰጠኝም ግን...

- አስፈላጊ ነገር በዓይን አይታይም... አለኝ።

- ነውና...።

- እንደ አበባይቱ ነው። ኮከብ ላይ ያለች አበባ ከወደድህ ሌሊት ጠፈሩን ቀና ብሎ ማየት ደስ ይላል። ከዋክብት ሁሉ በአበባ ተጊጠዋል።

- እኮ...።

- ውኃም ያው ነው። ያጠጣኸኝ ውኃ በመዘውሩና በገመዱ ምክንያት እንደ ሙዚቃ ነው ... ትዝ እንደሚልህ ... ጣዕሙ ልዩ ነበር።

- መች አጠጣሁት? ...

- ሌሊት ከዋክብትን ተመልከት። የኔይቱ ኮከብ በጣም ስለምታንስ አገሬም ጠባብ ስለሆነ ከዚህ ላሳይህ አልችልም። እንዲያውም ይኸው ይሻላል። የኔ ኮከብ ላንተ ከከዋክብቱ መካከል አንዷ ነች። ስለዚህ ከዋክብቶቹን ሁሉ ስታያቸው ደስ ይልሃል። ሁሉም ወዳጆችህ ይሆናሉ። በዚህ ላይ አንድ የምሰጥህ ሰጦታ አለ...።

እንደ ገና ሣቀ።

- አይ ማሞ፣ የእኔ ማሙዬ ፣ ይኸ አሣሣቅህ ደስ ሲለኝ!

- ይኸውልህ የኔ ስጦታ እሱው ነው ... እንደ ውኃው ነው ...

- ምን ለማለት ፈልገህ ነው?

- ከዋክብት ለሰዎች ሁሉ አንድ አይደሉም:: አንዳንዶች የሚጓዙ ሰዎች ኮከቦችን መሪዎቻቸው ያደርጓቸዋል:: ሌሎች ከብርሃን ብልጭታ ለይተው አያዩአቸውም:: በእውቀት ለላቁቱ ሰዎች ከዋክብት የጥያቄ ምልክቶች ናቸው:: እኔ ለተገናኘሁት ነጋዴ ወርቅ ናቸው:: ግን እነዚያ ከዋክብት አንድ ቃል አይወጣቸውም:: ላንተ የሚሰጡህ ከዋክብት ግን ለማንም ተሰጥተው የማያውቁ ናቸው::...

- ምን ማለት ፈልገህ ነው?

- ሰማዩን ሌሊት ስትመለከት እኔ ባንዱ ኮከብ ላይ ስለምኖር፣ እዚያ ላይ ሆኜ እሥቃለሁና አንተ ኮከቦች ሁሉ የሣቁ መስሎ ነው የሚሰማህ:: ያንተ ድርሻዎች የሚሥቁ ከዋክብት ይሆናሉ::

አሁንም ሣቀ::

- ስትጽናና (መጽናናት አይቀርምና) አውቀው ነበር ስትል ደስ ይልሃል:: ለዘለዓለሙ ወዳጄ ነው:: ከኔ ጋር ስትሆን ሣቅ ሣቅ ይልሃል:: አንዳንድ ጊዜም ዝም ብለህ መስኮትህን ትከፍታለህ፣ ለደስታ ያህል... ሰማይ ሰማይ እያየህም ስትስቅ ወዳጆችህ በጣም ይገርማቸዋል:: ያን ጊዜ፣ «አዎ ከዋክብት ሁልጊዜ ያሥቁኛል!» ብለህ ትመልስላቸዋለህ:: እነሱም አብዷል ብለው ያምናሉ:: አጉል ቀልድ ቀለድኩብህ ማለት ነው::

አሁንም ሣቀ::

- በከዋክብት ፋንታ አንድ አገር ሙሉ መሣቅ የሚያውቁ ቅጭልጭሎች የሰጠሁህ ያህል ነው...::

ይህን ብሎ እንደ ገና ሣቀ:: ወዲያው ኮስተር አለና፣

- ዛሬ ሌሊት... ገባህ... አትምጣ...::

- ጥዬህ አልሄድም::

- እንደ ታመመ ሰው ያደርገኛል... በመጠኑም እንደ ሞተ ሰው እሆናለሁ:: ይኸው ነው:: ይኸንን ለማየት አትምጣ ግድ የለም...

- ጥዬህ አልሄድም::

ግን ስጋት ገብቶታል::

- ይኸንን የምልህ ... በአባቡም ምክንያት ነው:: እንዳይነድፍህ ያስፈልጋል... እባብ ክፉ ነው:: ነደፋ ሊያስደስተው ይችላል:: ጥዬህ አልሄድም::

ሆኖም አንድ ነገር አረጋጋው::

- ሁለተኛ ጊዜ ሲነድፉ መርዝ የላቸውም...::

ያን ሌሊት ለመጓዝ ሲነሣ አላየሁትም:: ድምፁን አጥፍቶ ነው የኰበለለው:: ስደርስበት እርምጃውን ሳብ ሳብ የሚያደርገው በቀሩጠኛነት ነበር:: ንግግር ሳያበዛ ባጭሩ፣

- ታዲያስ ደረስክ ... አለኝ::

ከዚያም እጁን ያዘኝ:: ግን ጭንቀቱን ቀጠለ፣

- ልክ አይደለህም:: ታዝናለህ:: የሞትሁ እመስላለሁ እንጂ የእውነት አልሞትም...::

እኔ ዝም::

- ይገባሃል:: በጣም ሩቅ ነው:: ይኸንን ሰውነቴን ይገፍ መሄድ አልችልም:: በጣም ይከብዳል::

- እኔ ዝም::

- አርጅቶ እንደ ተጣለ ቅርፊት ይሆናል:: ያረጁ ቅርፊፊቶች አያሳዝኑም::


እኔ ዝም::

ትንሽ ተስፋ ቈረጠ:: ግን እንደ ገና አንሰራራና፣

- ጥሩ ይሆናል፣ ታውቃለህ:: እኔም ከዋክብትን አያለሁ:: ከዋክብቱ ሁሉ የዛገ መዘውር ያለባቸው ጒድጓዶች ይሆኑልኛል:: ከዋክብቱ ሁሉ የምጠጣው ውኃ ያንቆረቁሩልኛል::...

እኔ ዝም::

- በጣም ነው ደስ የሚለው! አንተም አምስት መቶ ሚሊዮን ቅጭልጭሎች፣ እኔም አምስት መቶ ሚሊዮን ምንጮች ይኖሩናል::...



ከዚያም እሱም ዝም አለ፣ እንባ አንቆት ነበርና...::

- ያው ደረስን:: ተወኝ አንድ እርምጃ ብቻዬን ልራመድ::

ፊርቶ ነበርና ቁጭ አለ::

ከዚያም እንዲህ አለኝ፣

- ታውቃለህ ... አበባዬ ... ኃላፊነት አለብኝ! በጣም ደካማ ነች! በዚህ ላይ የዋህ:: ዓለምን ለመቋቋም ያላት መሣሪያ አራት የማይረቡ እሾኾች ብቻ ናቸው...::



መቆም ስለ ተሳነኝ ቁጭ አልኩ::

እሱም፣

- ይኸው... በቃ... አለ::

አሁንም ትንሽ አንገራገረና ከተቀመጠበት ተነሣ:: አንድ እርምጃ ተራመደ:: እኔ መነቃነቅ አልቻልኩም ነበር::

ቀጥ ብሎ ቆመ:: ጩኸት አላሰማም:: እንደሚገረሰስ ዛፍ ቀስ እያለ ወደቀ:: እሸዋ ላይ ስለ ነበረ ሲወድቅ ድምፁ እንኳን አልተሰማም::

፲፯

አሁንማ እንግዲህ ስድስት ዓመት ሆነው:: ይህንን ታሪክ ለማንም ነግሬ አላውቅም:: ያገኙኝ ጓደኞቼ በሕይወት ስላገኙኝ እጅግ ደስ አላቸው:: እኔ አዝኜ ነበር ግን «ድካሙ ነው»... አልኳቸው:: አሁን በመጠኑ ተጽናንቻለሁ:: ቢሆንም... በሙሉ አይደለም::

ግን ወደ ሕዋ አካሉ መመለሱን በእርግጥ አውቃለሁ፣ ምክንያቱም ሲነጋጋ፣ ሰውነቱን አላገኘሁትም:: ይህን ያህል ከባድ አካል አልነበረም ... ሌሊት ከዋክብትን ማዳመጥ ደስ ይለኛል:: ድምፃቸው እንደ አምስት መቶ ሚሊዮን ቅጭልጭሌች ነው...::

እዚህ ላይ አንድ ታይቶ የማይታወቅ ነገር ደረሰ:: ለታዳጊው ልዑል እሳልኩለት መሸለቢያ ላይ የጠፍሩን ሽምቀቆ መሣል ዘንግቻለሁ! እበጉ አፍ ላይ ሊያስረው በፍጹም አይችልም ማለት ነው:: «ሕዋ አካሉ ላይ ምን ተፈጥሮ ይሆን» እያልሁ ራሴን እጠይቅ ጀመር:: ምናልባት በጉ አበባይቱን በልቶ ይሆናል...::

ወዲያው ደግሞ፣ «አይ በፍጹም! ታዳጊው ልዑል ማታ ማታ አበባዋን የመስታወት ክዳን ይከድንባታል፤ በጉንም በሚገባ



እንደሚገረሰስ ዛፍ ቀስ እያለ ወደቀ።

ይጠብቀዋል...::» ይህንን ሳስብ ደስ ይለኛል:: በዚህም ጊዜ ከዋክብቱ ሁሉ በቀስታ ይሥቃሉ::

አልፎ አልፎ በሆዴ ሳስብ፣ «አንዳንድ ቀን መዘናጋት አይቀርም:: ያን ዕለት አለቀ ማለት ነው! ወይ አንድ ቀን መክደኛውን ይረሳል፤ ወይ በጉ ሌሊት ድምፁን አጥፍቶ ይወጣል...::» ያን ጊዜ ቅጭልጭሉቹ ሁሉ ድምፃቸው ወደ ለቅሶ ይለወጣል! ...

ይኸ በራሱ ምስጢር አዘል ነገር ነው:: የት እንደ ሆነ ባልታወቀ ቦታ፣ አንድ የማናውቀው በግ አንድ ጽጌረዳ በልቷል ወይስ አልበላም የሚል ጥያቄ እስካልተነሣ ድረስ፣ ለናንተ ታዳጊውን ልዑል ለምትወዱትና ለኔም ጭምር፣ ፍጥረተ ዓለም ውስጥ ምንም ተመሳሳይ ነገር የለም ማለት ነው...::

ስማዩን ተመልከቱ:: «በጉ አበባይቱን በልቷል ወይስ አልበላትም?» ብላችሁ ራሳችሁን ጠይቁ:: ሁሉም ነገር እንዴት እንደሚለወጥ ታያላችሁ::...

መቼም ነፍስ ካወቁት ግለሰቦች መካከል አንዱም ይህ ጉዳይ ምን ያህል ታላቅ ቁም ነገር ያለበት መሆኑን አይገነዘበውም!

ተፈጸመ

